# **የመለስ “ትሩፋቶች”** (ባለቤት አልባ ከተማ)

**ደራሲ፤ ኤርምያስ ለገሰ**
**ቅኝት፤ መስፍን ማሞ ተሰማ**

***<u>መንደርደሪያ</u>***

በድሮ ዘመን የኖሩ እንስሳት እንዲህ ዘመሩ።

***የእንግሊዝ አራዊት፤***
***የአየርላንድ አራዊት፤***
***የየሀገሩ ሁሉ አራዊት፤***
***ተሳተፉ የደስታዬን ምንጩን፤***
***ስለመጪው ብሩህ ዘመን!***
***ይዘገያል ወይ ይፈጥናል፤***
***ያ! ቀን ግን ይመጣል፤***
***ጨቋኙ ሰው ይገረሰሳል! . . .***

ዘምረው ዝም አላሉም። ዘምረው አመፁ። አብዮት አፈነዱ፤ የእንስሳት አብዮት። በሚኖሩበት ሀገር - በእነሱ አጠራር፤ የእርሻ ጣቢያ - ለዘመናት በጭቆና ቀንበር ረግጦ ሲገዛቸውና ሲመዘብራቸው በኖረው የሰው ዘር ገዢያቸውና ግብረ አበሮቹ ላይ ሆ! ብለው ተነሱ። ቀንበር በቃን። ባርነት በቃን። ብዝበዛ በቃን። … ነፃነት እንጂ።

እነሆ አብዮቱ ድል ነሳ። ገዢያቸውና አበሮቹ ሸማና ነፍሳቸውን ይዘው ሸሹ፤ ተሰደዱ። የእርሻው ጣቢያም - ሀገራቸው የእንስሳቱ - የነሱ ሆነ። ስለ አብዮቱ የሰበኩት፤ የቀሰቀሱትና ያስተማሩት አሳሞች አስተዳደሩን ተረከቡ፤ ከነመዋቅሩ። እናም የእንስሳቱ ሀገር - የእርሻ ጣቢያው - *መንግሥት ሆኑ። አሳሞች ብቻ የሚመሩት መንግሥት።*

የአብዮቱን መርሆዎች - *እንስሳዊነትን* - የነደፉት አሳሞቹ ህገ መንግሥት ደነገጉ። ለእንስሳቱም ለራሳቸውም የሚሰራ። ሰባት ህግጋት። የማይጣሱ፤ የማይገረሰሱ። በአዲሱ የእንስሳት ሪፑብሊክ እስከ ወዲያኛው ፀንተው የሚኖሩ…

*እነሆ አሳሞቹ ውለው ሳያድሩ ህገ መንግሥቱን መጣስ መገርሰስ ጀመሩ። እንስሳቱም ተደናገሩ፤ ተደናገጡ። እንስሳቱ እንደተደናገሩ እንደተደናገጡ፤ አሳሞቹ በየደረጃው ህገ መንግሥቱን መናድ ቀጠሉ፤ ለሚንዱት እያንዳንዱ ህግ ማሻሻያ አንቀፅ እየጨመሩ።*

እንዲህ እያለ ዓመታት ነጎዱ። ህይወታቸው የእንስሳቱ ከድሮው ዘመን ቢብስ እንጂ አልተቀየረም። *አሳሞቹ ግና ሀብት በሀብት ላይ እያካበቱ ቶጀሩ፤ ደግሞም ታበዩ።*

እነሆ ተቃውሞ ተነሳ። የአሳሞቹ መንግሥትም - *ማንኛውም እንስሳ ሌላ እንስሳን መግደል የለበትም* - የሚለውን የህገ መንግሥቱን አንቀፅ ጥሶ ርሸና አካሄደ፤ አረመኔዎቹን ቅልብ ጠባቂ ውሾች አሰማርቶ። በቅልብ ጠባቂ ውሾች ደም ስራቸው የተነዘነጠለው እንስሳት የቀረበባቸው የክስ ቻርጅ - *አዲሲቷን የእንስሳት ሪፑብሊክ በማፍረስ ወደ ቀድሞው የሰው ዘር ሥርዐት ለመመለስ ማሴርና ህገ መንግሥቱን በሀይል ለመናድ ማመፅ* - የሚሉ ነበሩ። እናም በእንዲህ ያለ የደም ጎርፍ አብዮቱና ህገ መንግሥቱ ማጅራቱን ተመታ። እነሆ ፍፁማዊ የሆነ በዘረኝነት ላይ የቆመ አምባገነናዊና ዘረኛ *የአሳሞች መንግሥት* በእንስሳቱ ጫንቃ ላይ ተንፈራጠጠ፤ በእንስሳቱ ሀገር ፈላጭ ቆራጭ ሆነ።

ከጭፍጨፋው በኋላ በቀድሞው ዘመን፣ በአብዮቱ ድል ማግሥት፣ ተደንግገው የነበሩት ሰባቱ ህግጋት ተሸረው በአንድ ህግ ብቻ እንደሚተዳደሩ የአሳሞቹ መንግሥት አወጀ። በእኒያ ሁሉም እንስሳት ተስማምተውባቸው በነበሩት ህግጋት ውስጥ አንዱ እንዲህ ይል ነበር። "ሁሉም እንስሳት እኩል ናቸው!" እነሆ ሰባቱን ህግጋት የጨፈለቀውና የአዲሲቷ የእንስሳት ሪፑብሊክ መመሪያ የሆነው ብቸኛ ህግ እንዲህ ይላል፣ *"ሁሉም እንስሳት እኩል ናቸው። ነገር ግን ጥቂት እንስሳት ከሌሎች ይበልጥ እኩል ናቸው"*

*   *   *   *

ይህ እንግዲህ እንግሊዛዊው ደራሲ ኤሪክ አርተር ብሌር (ጆርጅ ኦርዌል) አኒማል ፋርም (የእንስሳት አብዮት) በሚለው *መፅሀፉ* በእንስሳት ተምሳሌ ስለህወሃት *መራሹ* የኢህአዴግ *መንግሥት* የነገረን ነው።

ኢትዮጵያዊው ደራሲ ኤርምያስ ለገሰ ሰዋዊ ባህሪ ስለተላበሰው ህወሃት መራሹ የኢህአዴግ *መንግሥት* "የመለስ ትሩፋቶች" *መፅሀፉ* ምን ብሏል? እናምራ ወደዛው......

## ክፍል አንድ

## *"መፅሀፈ ኤርምያስ"፣ ሥነፅሁፍዊ ፖለቲካ*

--------------//--------------

*"በተልዕኮና በኑሮ መካካል ያለው ግጭት አስቸጋሪ ነው። ተልዕኮ ያለው ሰው፣ ለዚያ ተልዕኮ ምቾቱን ብቻ ሳይሆን ውድ ህይወቱንም ጭምር አሳልፎ መስጠት አለበት። ታዲያ ተልዕኮ ያላቸው ሰዎች አብዛኛውን ጊዜ የሚጨነቁትና የሚያዝኑት ለራሳቸው ሳይሆን ለሚወዱዋቸው ሰዎች ነው። በኑሮና በተልዕኮ መካከል እስረኛ ከመሆን የበለጠ ጭንቀት ያለ አይመስለኝም። አንድ ደራሲ ወደ ኑሮ ካመዘነ የህይወት ቅጥረኛ ወይም አትራፊ ነጋዴ መሆን ይመጣል" በዓሉ ግርማ፣ 'ደራሲው' (1972 ዓ/ም)*

-------------//--------------

*"አሌፍ። በቁጣው በትር መከራ ያየ ሰው እኔ ነኝ። ብርሃን ወደሌለበት ወደ ጨለማ መርቶ ወሰደኝ። ቤት። ሥጋዬንና ቁርበቴን አስረጀ፣ አጥንቴን ሰበረ። ቅጥር ሰራብኝ፣ በሀሞትና በድካምም ከበበኝ። ቀድሞ ሞተው እንደነበሩ በጨለማ አኖረኝ። ጋሜል። እንዳልወጣ በዙሪያዬ ቅጥር ሰራብኝ፣ ሰንሰለቴን አከበደ።" ሰቆቃወ ኤርምያስ፣ (ምዕ.3 ቁ.1 — 7)*

-------------//----------------

### <u>1. የሁለት ነፍሶች ትንቅንቅ</u>



አስቀድሞ በኤርምያስ ትክለ ሰውነት ውስጥ ቀዳሚ ነፍስ ትኖር ነበር። እርሷም ቃለ - ጥምቀት ያደረገች፣ ለቃል የቀረበች *ደራሲ ነፍስ* ነበረች። እነሆ ከዓመታት በኋላ ይህቺ ነፍስ 'አብዮታዊ ዲሞክራሲን' በተጋተች፣ ለምዕዐት ዘመን በታጠቀች *ደባል ነፍስ* በለጋነቷ ታፍና፣ እግር ተወርች ተከርችማ፣ እንደበቷን ተሸብባ ከጨለማው አዘቅት ተጣለች። ቀዳሚት ነፍስ፣ ደራሲዋ ነፍስ፣ የቁራ ጩኸት ከዚያ ማዶ እየጮኸች ለዘመናት ማቀቀች...

ደባል ነፍስ በኤርምያስ ውስጥ ገዘፈች። *ሥጋውን አስረጀች።* አጥንቱን ሰበረች። *እነሆ ደባል ነፍስ ሠየጠነች። ሣጥናኤልን ከአራት ኪሎ አሽጋግራ እያየች - አመለከች። በግፍ ሠራዊት ተመልምላ የግፍ ሠራዊት ፈለፈለች። ኖረች፣ የጦቢያን ፍጥረት ኑሮ*

*እያመሰች። ግፍና ሀጢያትን ፅድቅ እያለች። ሰቆቃና እንባን - ፍሰሀ፣ ዋይታን - ደስታ፣ ውድመትና ጥፋትን - ለውጥ፣ ሞትን - ህይወት፣ ቅጥፈትን - ሀቅ፣ ምዝበራን - ልማት፣ አድልዖን - ፍትህ፣ ጨለማን - ብርሃን...እያለች፣ ደባል ነፍስ 'በአብዮታዊ ዲሞክራሲ' ተራቀቀች። በጦቢያ ላይ ታበየች። ዘመናትን አስቆጠረች፣ የግፍ ፅዋ ግፉዓንን እየጋተች።*

መቼም... አይነጋ የለምና ነጋ። ደራሲ ነፍስ፣ ቀዳማይ ነፍስ፣ ጊዜን በጊዜ ታግሳ፣ ቅጥፈትን በሀቅ አንቃ መቃብር ፈንቅላ ድምጿን አሰማች እሪ!! ብላ...ደባል ነፍስን እንጦርጦስ ዶላ.......ሃሌ ሉያ!

እነሆ የመለስ "ትሩፋቶች" - ባለቤት አልባ ከተማ!

## 2. ሥነ ፅሁፋዊ ምልከታ - ወፍ በረር

የታሪክ ምሁር አልያም ፖለቲከኛ ፖለቲካን ሲፅፍ ታሪክ ይሆናል። ፖለቲካን ደራሲ ሲፅፈውስ? ሥነ ፅሁፍና ፖለቲካ ተጋብተው - ሥነ ፅሁፋዊ ታሪክ ወይም ሥነ ፅሁፋዊ ፖለቲካ ይወለዳል። አብነት ቢሉ፣ "ኦሮማይ"ን ያቀርቧል።

የመለስ ትሩፋቶች፣ ፖለቲካ ነው። ታሪክ ነው። ሥነ ፅሁፍ ነው፣ ልብ ያልወለደው። ፖለቲካና ታሪክ ስለመሆኑ ማን ይሞግተናል? ሥነ ፅሁፍ ስለመሆኑ ግን ምሥክርነት እንሰጣለን፣ እንዲህ ብለን።

ቋንቋ፣ የቋንቋው አሰካክና አወራረድ፣ ገላጭነትና አርኪነት በራሱ ውበት ነው። ሥዕላዊ። ግዘፍ ነስቶ የሚታይ። ሲያነቡት አያታክትም። አይቆረፍድም። ያረካል። እዚያ ላይ ላለም፣ እዚህ ታች ለሚገኝም።

ገፀ ባህሪያት፣ 'የመለስ ትሩፋቶች' በሥነ ምግባራቸውና በባህሪያቸው እጅግ የሚያስደነግጡ፣ የሚያሰቅቁና የሚያሳፍሩ፣ በድንቁርና የተራቀቁ፣ በሴራ የተካኑ፣ በብቀላ የመጠቁ፣ አድነው የሚገድሉ - ገድለው የሚያድኑ፣ ተበላልተው የሚተካኩ፣ ተተካክተው የሚበላሉ፣ በህወሃት መራሹ ኢህአዴግ መንግሥት መለያ ገፀ ባህርያት የታጨቀ ነው። በመልዕክተ ኤርምያስ ገፀ ባህርያቱ አልያም ገፀ ጥፋቱ የተጋለጡበቱ አገላለጡ፣ መለ መላቸውን የወጡበቱ እንደው ባጭሩ - አጃኢብ ነው። ከገፅ ገፅ ሲላወሱ፣ ሲመሳጠሩ ሲገማገሙ፣ አኗኗራቸው ሰብዕናቸው ፍንትው ብሎ ጎልቶ ወጥቶ፣ አንባቢ ያያቸዋል፣ ያውቃቸዋል - ከቃላት መኻል ቦግ ብለው።

ሴራ፣ የመለስ 'ትሩፋቶች' ሴራ ሲቋጥር ሴራ ሲፈታ፣ ሴራ ሲፈለፍል የሴራ ኢንኩቤተር። መልዕክተ ኤርምያስ ታዲያ ይህንን ሴራ ሲነግረን፣ ሴራውን ሲያባዝት ሴራውን ሲፈታ፣ ደግሞ በሴራ ውስጥ ሴራ ሲያደራ...ሴረኞቹ ህወሃቱ/ኢህአዴጉ፣ ከማፍያ መፈልፈያ ሲሲሊያ ኢጣሊያ የመጡ እንጂ አይመስሉም የኢትዮጵያ ከኢትዮጵያ። ታዲያ የደራሲው ሥነ ፅሁፋዊ ክህሎቱ ባይታከል፣ እንደወረደ በመደዴ ቢፃፍ ኖሮ - የሴራው ጥልቀቱ፣ የክፋት ምጥቀቱ፣ የአድልዖው ልቀቱ...የህዝብ ሰቆቃ ንረቱ...የሀገር ምዝበራው ጡዘቱ...እየጠዘጠዘ እያስቃሰተ በቁጭት አብግኖ የማንተክተክ ሃይሉ ለሥርዐቱ ተቃዋሚም ሆነ አጥር ላይ ለቆሙት እኩል ብርታት አይኖረውም ነበር። ለሥርዐቱ ተሟጋቾችም ቢሆን ትንፋሽ ወስደው ቆም ብለው ዞረው እንዲያሰላስሉ የማድረግ ብቃቱ ብርቱ ነው። 'እንገት የተፈጠረው ዞሮ ለማየት ነው' እንዲል ብሂሉ። መፅሀፈ ኤርምያስ ይህንን የማድረግ ሃይል አለው።

ግጭት፣ የመለስ 'ትሩፋቶች' ባለቤት አልባ ከተማ ታሪክ የኢትዮጵያ ህዝብ ትግል ታሪክ ነው። ህወሃት/ኢህአዴግ ሰጥ ለጥ አድርጎ ለመግዛት፣ ህዝብ በአምባገነናዊና አፓርዳይዳዊ መንግሥት ላለመገዛት ያደረጉት ትንቅንቅና ትግል ታሪክ። ምርጫ 92፣ ምርጫ 97 ምርጫ 2000። በአንፃሩ ይህ መፅሀፍ የሥርዐቱን አራማጆች የእርስ በርስ

መጠላለፍ፤ መገማገም፤ ገድሎ ማዳን እና አድኖ መግደል ታሪክ ከዚህ ቀደም ባልተነገረ መልኩ የዘረገፈ ዶሴ ነው። የፍርድ ቤት ኤግዚቢት!! ቀን ሲወጣ ፍትህ ማማ ላይ ምሥክርነት የሚቆም…

ጭብጥ፤ ጭብጡማ ያው 'ትሩፋቶቹ' ናቸው። በመልዕክተ ዜናዊ ተበጥብጦ በአብዮታዊ ዲሞክራሲ ሰንኬሎዎች የተጋትናቸውና በዘመነ ፍዳ ገና ያልጨረስናቸው።

እነሆ የመልዕክተ ኤርምያስን ሥነ ፅሁፋዊ ይዘት ምልከታ በዚሁ እንግታና ወደ ታሪኩ እናቅና።

## ክፍል ሁለት

## የአብዮታዊ ዲሞክራሲ 'ትሩፋቶች'

<u>**እንደ መነሻ፤**</u>

በኢትዮጵያ የአሜሪካን አምባሳደር የነበሩት ዶናልድ ያማማቶ ኦገስት 1/2008 (እኤአ) ለስቴት ዲፓርትመን በላኩት ኬብል ውስጥ ስለ "አብዮታዊ ዲሞክራሲ" እንዲህ ብለዋል፤

*"በትግራውያን የተዋጠው የማዕከላዊና የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት ፅንፈኞች ቢሆኑም ብዙዎቹ አሜሪካንን የሚቃወሙ አይደሉም። ኢህአዴግ በኢትዮጵያ መንግሥታዊ መዋቅራት ሁሉ ቁጥጥሩንና የበላይነቱን ይዞ የመዝለቁን ጉዳይ የቆረቡበት ናቸው። እንደ ስብሃት ነጋ፣ አባዲ ዘሞ እና ሌሎችም ከፅንፈኛው ክፍል የሚመደቡ ናቸው።*

*"አብዮታዊ ዲሞክራሲ በሚለው መርሃቸው ሁሉም የሚጋሩት የጋራ አጀንዳ አላቸው። ይህም በቁጥጥራቸው ሥር በሚገኙት መንግሥታዊ መዋቅራት /ኢኒንቲቱሽንስ/ ሁሉ አስተሳሰባቸውን (አብዮታዊ ዲሞክራሲን) በማስረፅ መምራት ነው። ሁሉም አምባገነኖች ናቸው።"*

አምባሳደሩ በኢትዮጵያ ቆይታቸው አብዮታዊ ዲሞክራሲን ከውጪ ወደ ውስጥ የገመገሙበት መነፅር የብዝበዛ የአምባገነንነትና የዘረኝነት መመረያ ንድፈ ሀሳብ መሆኑን የመሰከሩበት ሆኖ ይገኛል።

የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ መለስ ዜናዊ ከኢትዮጵያ ፖለቲካ ምህዳር ሲጠፉና መኖር መሞታቸው ሲያነጋግር በነበረበት ወቅት አቶ ግራሃም ፒብልስ - ለሰው ልጆች መብት ለውጥ የሚታገለው ዓለም ዐቀፍ ድርጅት ዳይሬክተር - ኦገስት 15/2012 (2004 ዓ/ም) ለንባብ ባበቁት ሰፊ ፅሁፋቸው ደግሞ ስለ አብዮታዊ ዲሞክራሲ ያነጠቡትን እንዲህ ያነቧል፤

*"ኢህአዴግና መሪው መለስ ዜናዊ በህገ መንግሥቱና በፌዴራል ደንብ ውስጥ የዴሞክራሲን ዋጋ /ቫልዩ/ እና የሠብዓዊ መብቶችን ህግ ጨምሮ የተቀበሉ ለመሆናቸው በአደባባይ የፈረሙበት ጉዳይ ቢሆንም - ይህ ከወረቀት ህግና ደንብነት ውጪ በተግባር ግን እንዳለ ተደምስሶ 'በአብዮታዊ ዲሞክራሲ' አይዲዮሎጂና መርህ ተተክቶ ይገኛል። አብዮታዊ ዲሞክራሲ ማለትም የግለሰብ አስተሳሰብ ነፃነትን ገፍፎ ሁሉም ሰው እንደ አንድ ሰው የሚያስብበት የመንጋ አመለካከትን በማስፈን በተማከለ /ሴንትራላይዝድ/ አገዛዝ ሥር ለመምራት የሚያስችል ዶግማ /ቀኖና/ ማለት ነው።*

*"የሠብዐዊ መብት ጠባቂ /ሂዩመን ራይትስ ዎች/ 'ዕድገት ያለ ነፃነት' /ዴቨሎፕመንት ዊዝ አውት ፍሪደም/ በሚል ርዕስ ባቀረበው ሪፖርት የአቶ መለስን የዲሞክራሲያዊ አይዲዮሎጂ አመለካከት በራሳቸው አንደበት የተናገሩትን ሲጠቅስ -*

*ግለሰቦች ሁሉ አስተሳሰባቸው አንድ ወጥ ሆኖ እያንዳንዱ ሰው የራሱ የሆነ ግላዊ አመለካከት ወይም አስተሳሰብ አይኖረውም። በዚህም መስመር የግለሰብ አስተሳሰብ የወል ወይም የጋራ አስተሳሰብ ይሆናል። ምክንያቱም አንድ ግለሰብ በአብዮታዊ ዲሞክራሲ ፅንሰ ሀሳብ መሰረት ያልተሰጠውን ሀሳብ ማፍለቅ ወይም ማንፀባረቅ አይችልም - ነበር ያሉት።”*

እነሆ ከዚህ በላይ ባቀረብኳቸው ምልከታወች የምናነጥረው ሀቅ፤ አብዮታዊ ዲሞክራሲ የግለሰብ አስተሳሰብን ወቅሮ የመንጋ አስተሳሰብን በማስፈን የመምራት/የመግዛት ‘ትሩፋትን’ ያስገኘ የህወሃት/ኢህአዴግ አዚመኛ ‘ዳዊት’ መሆኑን ነው። ይህ ከውጪ ወደ ውስጥ ያየነው ፅልመታዊ ገፅታ ከውስጥ ወደ ውጪ በመፅሀፈ ኤርምያስ እንደምን ተነግሯል? እነሆ ከሰፊው ባህር እንደሚከተለው ተጨልፏል።

## ዶን ቦስኮ

*በላፍቶ ሳር ቤት አካባቢ በጫካና ወንዝ የተከበበው ዶንቦስኮ የሥርዐቱ ዋነኛ መጨቆኛ ቦታ ነበር። በመዲናይቱ ካድሬ ሆኖ ለመመደብና የመንግሥት ሥልጣን ላይ ለመቆየት በየጊዜው ዶንቦስኮ እየተገባ መሰልጠንና መገምገም ግዴታ ነበር። ለመጀመሪያ ዙር ለሁለት ወራት በአዳሪነት መሰልጠን የማይታለፍ ነው።*

*የዶንቦስኮ ካሪኩለም ትኩረት በአብዮታዊ ዲሞክራሲ መርሆዎች ላይ ነበር። መስቀለኛ መንገድ ላይ የነበረችውን ኢትዮጵያ ኢህአዴግ እንዴት እንደታደጋት፤ የብሄርና መሬት ጥያቄ፤ ዲሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት፤ ጠባብና ትምክህተኝነት ዋነኛ አጀንዳዎች ናቸው።*

*ዶንቦስኮ በታቀደ መልኩ የከተማውን ካድሬዎች ወኔ ለመስለብ የተዘጋጀ መጨቆኛ ተቋም ነበር። ካድሬዎችን አስቀድሞ በማደንዘዝ ምንም ጥያቄ እንዳያነሱ፤ የህዝቡን ብሶት ተጋርተው እንዳያስተጋቡት ከወዲሁ እንደ እባብ አናታቸውን ለመቀጥቀጥ በማሰብ የተዘጋጀ። የከተማው ካድሬዎችና የመንግሥት ባለሥልጣናት በፍርሃት ሥጋት እንዲሞሉ ለማድረግ፤ ፀጥ ለጥ ብለው እንዲገዙ፤ አቅመ ቢስ እንዲሆኑና የራሳቸውን ጥላ ሳይቀር እንዲጠራጠሩ የተቋቋመ ተቋም። ይህን ለማስፈፀም ቅድመ ዝግጅቱ አስቀድሞ ይጀመራል።*

አጀብ ዶንቦስኮ። ኤርምያስ የዶንቦስኮ አብዮታዊ ዲሞክራሲ ጥርነፋ ውጤት ነበር። በዶንቦስኮ ተጠርንፎ ለአስራሁለት ዓመት ወኔው ተሰልቦ፤ የህዝብን ብሶት አላየሁም፤ ብዝበዛውን አላውቅም ብሎ የኖረ ካድሬና ሚኒስትር። እሱም በተራው ሌሎችን ዶንቦስኮ ወስዶ የጠረነፈ። እሱስ ተገላገለ። እነዛስ፤ በእርሱ የተመለመሉት የአብዮታዊ ዲሞክራሲ ዘማቾች (እርሱው እንደነገረን) አስር ሺዎቹ? ምናልባት “የመለስ ትሩፋቶች” እንደ ጋሪ ፈረስ የተጋረደ ዓይናቸውን ግርዶሹን አስጥሎ፤ ዳባ የለበሰ ጆሯቸውን ከፍቶ፤ የገነተረ ልባቸውን ልብ ሰጥቶ - ወደ ህዝብ እምብርት ይመልሳቸው ይሆን? ተስፋ እናደርጋለን፤ ሁሉን ባይሆን ከድንዘዛ የተረፈ ህሊና ያላቸውን!

ኤርምያስ ጀባ ያለን የዶንቦስኮ ታሪኮች አስደማሚ ብቻ ሳይሆኑ አሳዛኝም አሳፋሪም ዘግናኝም ናቸው። የሥርዐቱን ልቃቂት የጎለጎሉ። እንዲህ ይላል ኤርምያስ፤ *እንደ ዕውነቱ ከሆነ ዶንቦስኮ ፆታና ዘር ሳይለይ ጨርቅ አስጥሏል። በስልጠና ላይ እያለ ከተኛበት ዶርም በሌሊት ልብሶቹን አውልቆ ወንዝ ሊገባ ሲል የተያዘ ባለሥልጣን ነበር። የምን ማስተርስ በማለት ፈረንጅ ሀገር ያገኘውን ዲግሪ የቀዳደደም እንዲሁ።*

*መጀን ለዶንቦስኮ፤ መጥኔ ለአብዮታዊ ዲሞክራሲ ቀጣይ ተጠርናፊዎች!* በዚህ ንዑስ ቅኝት መፅሀፈ ኤርምያስ ስለዶንቦስኮ የዘከዘካቸውን ጉዶች መቀንጨብ እንኳ አንደፍርም። ታሪኩን ወዘና ያሳጣዋልና፤ መፍትሄው ወደ ምንጩ ወርዶ መኮምኮም ነው፤ ጉዱ እስኪያስገሳ።

በዘመኑ ደርግ ካድሬ ማምረቻው 'የካቲት 66 የፖለቲካ ት/ቤት' ይባል ነበር። ይህ ት/ቤት በማርክስና ሌኒን ፍልስፍና ከማጥመቅ ውጪ በዶንቦስኮ እንደተነገረን ያለ ዘግናኝ ትርዒትና ድራማ የሚካሄድበት እንዳልነበረ በደርግ ዘመንም ሆነ በተለይም ከደርግ ውድቀት በኋላ በወጡ ፅሁፎች መረዳት ይቻላል። ነገር ግን ስለዶንቦስኮ እንጠይቃለን፤ እንዲህ ብለን። ለመሆኑ 'ዶንቦስኮ' ከየት የተቀዳ ስም ነው? ለምን?? መፅሀፉ ኤርምያስ በዚህ ዙሪያ የሰጠን መልስ የለም፤ እኛው እንመልሰው።

ዶንቦስኮ ጣሊያናዊ ነው፤ የካቶሊክ ቄስ። በ1815 በፒድሞንት ጣሊያን ተወልዶ በ1888 ቱሪን ጣሊያን በ72 ዓመቱ አረፈ። ሙሉ ስሙ ጂዮቫኒ ሚሊኪዮሪ ቦስኮ ይባላል። ጂዮቫኒ ህዝባዊ ስሙ ዶንቦስኮ ነው። ዶንቦስኮ ፀሀፊና መምህር ሲሆን የሚታወቀውም ችግረኛ፤ መንገድ ተዳዳሪና ምፅዋተኛ ወጣቶችን አሰባስቦ በመርዳት ነው። ዶንቦስኮ ከቅጣት /ፓኒሽመንት/ ይልቅ በፍቅር ላይ የተመሰረተ አስተምህሮ በመቀየስ በ1876 በስሙ የሚጠራ ማህበር አደራጅቶ ተንቀሳቀሰ። ዛሬ ይህ ዶንቦስኮ በመባል የሚጠራው ተቋም በተለያዩ ሀገራት ውስጥ የሚገኝ ሲሆን የወጣቶች መዝናኛ ስፍራዎችን በማቋቋምና በመምራት ይታወቃል።

ለመሆኑ በላፍቶ የሚገኘው የአብዮታዊ ዲሞክራሲ ማጥመቂያ ተቋም ካልጠፋ ሀገርኛ ቋንቋ ይህንን የጣሊያን ስም ስለምን መታወቂያው አደረገ? ሊተላለፍን የተፈለገው መልዕክት ምን ይሆን? ምናልባት የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ውስጥ መውደቃችንን በእጅ አዙር ቋንቋ ህወሃት እየነገረን ይሆን?....አብላጫው ግምት ሊሆን ይችላል። ለማንኛውም ዶንቦስኮን በዚሁ እንሰናበት። በአብዮታዊ ዲሞክራሲ ላይ ግን ጥቂት እናዝግም።

**እነሆ መፅሀፉ ኤርምያስን እንጠቅሳለን።**

***አብዮታዊ ዲሞክራሲ ለብዙዎቹ የህወሃት ታጋዮች ምድራዊ ሃይማኖት ነው። ከኢትዮጵያ ውጪ በየትኛውም ሀገር የሌለ። በታሪክ አጋጣሚ ደግሞ መንግሥታዊ ሃይማኖት ሆኗል። ይህን ሃይማኖት የፈጠሩት ሰዎች ተከታዮቻቸው ሲበሉም ሲጠጡም፤ ሲተኙም (በህልማቸው ሳይቀር) እንዲያስቡት አድርገው ቀርፀውታል። ሌላው ቀርቶ የግል ህይወት ውስጥ ችግር ሲያጋጥም፤ ሀዘን ሲደርስ፤ ትዳር ሲመሰረት እንኳን በዛ ቅኝት መሆኑን ማረጋገጥ ይፈልጋሉ። ለዚህ መከራከሪያ ሩቅ መሄድ ሳያስፈልግ ብዙዎቹን የህወሃት ታጋዮች ጠጋ ብሎ "ሚስትህን እንዴት አገባኻት?" ብሎ መጠየቅ በቂ ይሆናል። ታጋዩም ሳያቅማማ "አብዮታዊነቷና የዓላማ ፅናቷ ማርኮኝ!" የሚል ምላሽ ይሰጣል።***

*ከእለታት አንድ ቀን የኢህአዴግ ቢሮ የሥራ ባልደረባዬ ይሳቅ ቆሪጥ (ዘመን ተሻጋሪው ካድሬ) ቢሮዬን ከፍቶ ሲገባ ደስተኛ ያልሆነ መልኬን ተመለከተ። ለምን እንደተበሳጨሁ አጥብቆ ጠየቀኝ። ከሚስቴ ጋር አለመግባባት ተፈጥሮ እንደተበሳጨሁ ነገርኩት። ታጋይ ይሳቅ ለአንድ ቀን ሙሉ መልዕክተ ዜናዊን ምዕራፍ በምዕራፍ* ***እየገለጠ አስተማረኝ።*** *ትምህርቱን እንዲህ በማለት አጠቃለለ፤*

*ችግር ያጋጠመህ ትዳርህን አብዮታዊ ዲሞክራሲ ባስቀመጠው ትዕዛዝና ቅኝት ስላልመራኸው ነው። እኔና ሚስቴ ተሳስበን በፍቅር የምንኖረው አብዮታዊ ዲሞክራሲ ባስቀመጠልን መስመር ስለምንሄድ ነው። አለመግባባት እንኳን ቢፈጠር አብዮታዊ ዲሞክራሲ ያስቀመጠልንን የችግር መፍቻ አቅጣጫዎች እንጠቀማለን። በየሳምንቱ እሁድ ልጆቻችንን አስቀምጠን በሀዲዱ ላይ መጓዛችንን እናረጋግጣለን። ለዚህ ያደረሱን መስዋቶች ዘላለማዊ ክብር እናጎናፅፋለን።*

*ይህ የይሳቅ ምክር የመቶሺዎች ነው። የህወሃት ታጋዮች አብዮቱን የሚያወድስ ኢታሞ በተደለቀ ቁጥር አቅላቸውን ስተው ይወድቃሉ። በእንባ ይራጫሉ። በትጥቅ*

*ትግሉ የሞቱ ጓዶቻቸውን ስም እየጠሩ ሰማዕትነታቸውን ይዘክራሉ። አስተሳሰቡ የበላይነት እንዲያገኝም ተግተው ይሰራሉ።*

***እንግዲህ ይህ አመለካከት ነው በትጥቅ ትግል አሸንፎ መንግሥት የሆነው። መንግሥት ሆኖም መሰረታዊ ባህሪው የሆነው የዜሮ ድምር ጨዋታ አልተቀየረም። በኢትዮጵያ ምድር አብዮታዊ ዲሞክራሲ እያለ ስለ ክርስትና እስልምናና ሌሎች ሃይማኖቶች እኩልነትና ነፃነት ማሰብ የማይቻል መሆኑን ነው። ርግጥ ሌሎች ሀይማኖቶች ከአብዮታዊ ዲሞክራሲ በፊት የተፈጠሩ በመሆናቸውና የብዙሃኑ የህይወት መመሪያ በመሆናቸው ሊያጠፋቸው አይችልም። ያለው ብቸና አማራጭ መንግሥታዊ ሥልጣኑን ተጠቅሞ ማዳከምና ችግር መፍጠር ይሆናል።***

***አብዮታዊ ዲሞክራሲ መራሹ መንግሥት የሚፈጥራቸው ችግሮች መጠነ ሰፊ ናቸው። ከእነዚህም ውስጥ ለአንዱ ሃይማኖት ወገንተኛ መስሎ መታየ፣ ተቋማቱ እርስ በርስ ተራማጅ ያልሆነ ፉክክር ውስጥ እንዲገቡ…እርስ በርስ በጠላትነት እንዲተያዩና የጡንቻ ፍተሻ ውስጥ እንዲገቡ ማድረግ…***

ይህ እንግዲህ የመፅሀፊ ኤርምያስ ኑዛዜ ነው፤ ቀድሞ የአብዮታዊ ዲሞክራሲ ዋና ካድሬና ሚኒስትር ደኤታ ኑዛዜ። ሁለት አስርታትን ሰልቅጦ ሶስተኛውን ሊሰለቅጥ የሚንደረደረው ኢትዮጵያን ያጠለማት የአብዮታዊ ዲሞክራሲ መንፈስ በመቶ ሺዎች ብቻ ሳይሆን በሚሊዮናት የሚቆጠሩ የአብዮታዊ ዲሞክራሲ ዛር የሚያንዘፈዝፋቸው ዜጎች ያለመታከት ይፈለፍላል። በዜግነት፣ በዘር፣ በሀገር፣ በሃይማኖት፣ በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚ፣ በማህበረሰብ ህይወት…ውስጥ የዘለቀውን የዚህን ዛር ጥልቀትና ምትሃት ደግሞ መፅሀፊ ኤርምያስ ሲተረትረው…ቀዝቃዛ ላብ በጀርባችን ይወርዳል…የዚህ መንግሥት ዕድሜ መርዘም በአራቱም ማዕዘን የማጡን መስፋት እያሳየን። ምን ይሻላል?!

<u>ዜሮ ድምር ምንድር ነው?</u>

ኤርምያስ ይመልስልናል፤ *ከኢህአዴግ የግምገማ ስልቶች ስራ ላይ የሚውለው "ገሎ ማዳን" እና "አድኖ መግደል" በመባል ይታወቃሉ። ሁለቱም የዜሮ ድምር መጫወቻ ቴክኒኮች ናቸው።* ***አንዱን ለማዳን ሌላውን መግደል። የአብዮታዊ ዲሞክራሲ ጨዋታ!***

*የዜሮ ድምር ጨዋታ እንደ ኢኮኖሚክስ ባሉ የማህበረሰብ ሳይንሶች ከተለመዱ ህልዮቶች አንዱ ነው። በዚህ የጨዋታ ህግ መሰረት አንዱ ሙሉ ለሙሉ ለማሸነፍ ሌላኛው መሸነፍ፣ አንደኛው ሊያተርፍ ሌላኛው መክሰር፣ አንዱ ሊበለፅግ ሌላኛው መደህየት አለበት። በዜሮ ድምር ጨዋታ የጋራ ድል የሚባል ነገር አይሰራም። ዋነኛው ባህሪው ጥሎ ማለፍ ነው።*

***አቶ መለስ የዜሮ ድምር ጨዋታ መሀንዲስ ነበር። መቼና በምን መልኩ እንደሚተገብረው ይቀይሳል…***

*መፅሀፊ ኤርምያስ ተቆጥረው የማያባሩ የዜሮ ድምር ድራማዎችን* በ408 ገፆች ውስጥ እንደጤፍ ዘርቷቸው እናገኛለን። የአብዮታዊ ዲሞክራሲ መሪዎች ከዜሮ ድምር ውጪ የሚያስቡትና የሚተገብሩት መኖሩ ያጠራጥረናል። ቲያትሩን እንደምን አድርገው ፅፈው ተዋንያኑን እንደምን እንደሚያስተውኑ ስንመለከት ደግሞ አግራሞታችን ወደር አይኖረውም። አንዳንዴም ራሳቸው ፀሀፊና ተዋንያን ሆነው እናገኛቸዋለን፤ መሀንዲሱን መለስ ጨምሮ። 'አዜ' መለስን በመሀንዲስነቱና በመድረክ ዳይሬክተርነቱ የሚስተካከለው ባይኖርም ተቀጥላዎቹም የዋዛ አለመሆናቸውን ከጨፌው የአዲስ አበባ ፕሬዚዳን አሊ አብዶ ግምገማ (1995 እስከ 2000ዓ/ም) ጀምሮ ትርክቱን ወደፊትና ወደሁዋላ (በምልሰት የአፃፃፍ ቴክኒክ) እንደ ፔንዱለም እያመላለሰ ያወጋን መፅሀፊ ኤርምያስ ገለታ ይድረሰውና ብዙ ታሪክ፣ ብዙ ድራማዎች እጅና እግራቸውን እንድናይ

አድርጎናል። ከዜሮ ድምር (ገድሎ ማዳን ወይም አድኖ መግደል) ተውኔቶች - ከሰፊው ጎተራ - ሁለቱን ለአብነት ብናቀርብስ?

አነሆ አስቀድሞ እግዜሩን እናቀርባለን፤ *ገብረ እግዚአብሄር 'እግዜሩ' ነባር የህወሃት ታጋይ ነው። መጠሪያውና ግብሩ ለየቅል የሆነ ሰው! አንዳንዴ ስምን ሰይጣን ያወጣዋል።* በማለት ይጀምራል ደራሲው። ከፊል ታሪኩን (ሙሉውን ማቅረብ ስለማንችል) እራሱ ይተርክልናል፤ እሳት ዳር ተቀምጠንም ባይሆን ባለንበት፤ እነሆ ኤርምያስ ይቀጥላል፤

*የካዛንችሱ ስውር መንግሥት ለእግዜሩ ተነግረው የማያልቁ ወንጀሎችን እንዲሰራ ሙሉ ሥልጣን ሰጥቶት ነበር። እግዜሩ በሥርዐቱ ውስጥ ካሉት ሶስት ቁልፍ የዞን ካድሬዎች አንዱ ነበር። መቀመጫውን ሜክሲኮ በማድረግ ሰቅጣጭ ግፎችን ሰርቷል። ብዙ ሰዎችን ያለወንጀላቸው አሳስሯል። ከስራ አባሯል። አገር ጥለው እንዲወጡ አድርጓል። የግለሰቦችን፤ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ቢሮዎችን በሌሊት በመክፈት አስበርብሯል። ዶክመንት ኮፒ አድርጎ አውጥቷል።*

***እግዜሩ በዞኑ ውስጥ የሚገኙና ጥብቅ ክትትል የሚደረግባቸውን ተቋማት ማስተር ቁልፍ በማዘጋጀት ዶክመንቶችን ያሰርቃል። ኮፒ ያስደርጋል። ቢሯቸው እንዲሰበር ካደረጋቸው ውስጥ በወረዳ 21 ፅ/ቤት ግቢ ውስጥ የሚገኘው የአዲስ አበባ ሴቶች ፅ/ቤት ማህበር፤ የልደታ ቤተ ክርስቲያንና የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ጉባኤ (ኢሰመጉ) ይገኙበታል። የአዲስ አበባ ንግድ ምክር ቤት ከእግዜሩ የስለላ ወጥመድ ማምለጥ አልቻለም። የንግድ ምክር ቤቱ የተወያየባቸው አጀንዳዎችና ቃለ ጉባኤዎች በቀጥታ ይደርሱታል።***

እውነትም 'እግዜሩ' እንደ ስሙ ሳይሆን ምግባሩ እንደ ሸይጣኑ ነው። መፅሀፈ ኤርምያስ ስለ ካዛንችሱ መንግሥት በአያሌ ገፆች የዘከዘካቸው ሰቆቃዎች፤ እውነት እላችኋለሁ፤ የልብ ምት ያፈጥናሉ፤ የሌሊት እንቅልፍ ይረብሻሉ፤ ያስቃዥሉ። የእነ አሊ አብዶ ሥራ ሀገር ምድሩን አሳብዷልና... የሸይጣኑም ሥራ እንዲሁ። አነሳሳችን በዜሮ ድምር ዙሪያ ስለሆነ 'እግዜሩን' አልያም 'ሸይጣኑን' ከዚህ ጋር ወደሚያገናኘው ሰበዝ እንሻገራለን፤ ሌላውን ለመፅሀፉ ታዳሚ ለቀን። ኤርምያስ ይቀጥላል፤

*እግዜሩ የካዛንችሱ መንግሥት ሲንኮታኮት አብሮ ወደቀ። በአዲስ አበባ የእነ ተወልደን ቡድን በመደገፍ ቀንደኛ ሆኖ ወረቀት የበተነውና ካድሬውን በፀረ - መለስ ያደራጀው እሱ እንደሆነ ሞንጆሪኖ አጋለጠች። የህቡዕ አደረጃጀቱ ማታ ማታ ስብሰባ ሲያደርግ የነበረው በሜክሲኮ እንደነበረ ተረጋገጠ። ማምለጫ መንገድ ሲያጣ አቶ መለስን ይቅርታ ጠየቀ። አቶ መለስ እንደ ሌሎቹ አልራራለትም። "በዛገ ቢለዋ የድርጅቱን አንገት ዘክዝከኻል" ብሎ በቅጣት መልክ የትግራይ በረኻ ሰደደው።*

*እግዜሩ ለሶስት ዓመት ያህል የትግራይ ተራራን ሲቧጥጥ ከረመ። መስመር ማስተካከሉና እርምት መውሰዱ ሲረጋገጥ የተዘጋጀለት የሙስና ፋይል በጎን እንዲደርሰው ተደረገ። "ሲያዩህ ሌባ ትመስላለህ" ብሎ እንዳላባረረ የርሱ ንቅዘት የማያልቅ ሆኖ በፋይል ተጠርዞ ተሰጠው። በየዓመቱ በሚሊዮን ብሮች የሚዘረፍበትን የአየር ጤና ኬላ (ጉምሩክ) ህሩይ የሚባል የቅርብ ዘመዱን ሃላፊ አድርጎ ሲያሰራ እንደነበር፤ ሲኖርበት የነበረውን የቀበሌ ቤት ለወንድሙ ስም አዞሮ መስጠቱ፤ ኤርትራውያን ናችሁ በማለት በግፍ ከቪላ ቤታቸው ካፈናቀለ በኋላ እሱ ገብቶበት መኖር እንደጀመረ፤ በምርጫ 97 ማግስት ኮልፌ ቀራንዮ ላይ አርከበ እቁባይ አይን መሬት እንደሰጠው።*

*እናም እግዜሩ ይህንን የታሸገ የሙስና ፋይል ይዞ አዲስ አበባ መጣ። አቶ መለስ የኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን የትግርኛ ፕሮግራም ዋና ሃላፊ አድርጎ ሾመው።*

*የአድርባይ ፊታውራሪ ከሆነው ዘርዓይ አስክዶም ጋር ተቀላቀለ። የኢቲቪ የትግርኛ ፕሮግራም ከእንጨትነት ወደ 'አሞራ ሥጋነት' ተቀየረ። እምብር ተጋዳላይ!!*

እነሆ የዜሮ ድምር ጨዋታ ጥርሱን አግጥጦ አይኑን ጎልጉሎ በመሀንዲሱ አቶ መለስ ተግባር ላይ ውሎ። ሽይጣኑ የፈፀማቸውን ወንጀሎች ሁሉ በፋይል ጠርዞ የላከለት ድርጅቱ ህወሃት/ኢህአዴግ ነው። እግዜሩ ወይም ሽይጣኑ (በኛ አጠራር) ወንጀለኛ ነው። የዘረፈው ተመልሶ፣ ለሰራቸው ወንጀሎች በእግረ ሙቅ ታግቶ ቃሊቲ በእድሜ ልክ እስራት መውረድ የነበረበት ወንጀለኛ። ነገር ግን የሽይጣኑ ወንጀሎች፣ የፈፀማቸው ግፎችና የዘረፈው ንብረት ለአቶ መለስ ደንታ አልሰጡትም። አቶ መለስን ያንገበገበው እግዜሩ/ሽይጣኑ በእሱ ላይ ማሴሩ ብቻ ነበር። እና አቶ መለስ እግዜሩ ስላደመበት ገደለው። ገድሎ አዳነው፣ በአብዮታዊ ዲሞክራሲ መርሆ!! ሽይጣኑ የነስዬን ቡድን በመቀላቀሉ ወደ ግዞት ላከው፣ የቁም ሞት እንዲሞት። በቁም እየሞተ ባለበት የሙስና ፋይል መሀንዲሱ ላከለት። እግዜሩ ላይ ሽምቀቆ አጠለቀለት። ሽምቀቆውን እንዳንጠለጠለ ሽይጣኑ አዲስ አበባ መጣ። አቶ መለስ ሾመው። ገድሎ አዳነው። እግዜሩ አንገቱ ላይ የገባለትን ሽምቀቆ (የሙስና ፋይል) በየደቂቃው እያስታወሰ፣ እንግዲህ እድሜ ልኩን ይበልጥ ሰይጥኖ ድርጅቱን ይታደጋል፣ ዜሮ ድምር ሥራውን ጨርሷልና!

ቀጥሎ የምናቀርበው የዜሮ ድምር ጨዋታ ሞንጆሪኖን ይመለከታል። ለማመጣጠን። ማመጣጠን የአብዮታ ዲሞክራሲ መቆመሪያ ቃል ነው። ከነሱው ነው የተዋስነው። ሽይጣኑን ካቀረብን አይቀር ሽይጣኒቱንም ለማቅረብ፣ በማመጣጠን ስሌት። መልዕክተ ኤርምያስ እንዲህ ተላልፏል።

*ሞንጆሪኖ አታረጅም።*

*ሁልጊዜም ወጣት ናት። ማንም አይቷት አስቸጋሪውን የዱርና ቆንጥር ዘመናት አሳልፋለች ብሎ ማመን አይቻለውም። ተራራን ያንቀጠቀጠች ቋጥኝ የደረመሰች አትመስልም። የእጆቿ ልስላሴ ከብዙዎቹ ተጋዳሊቶች የተለየ ነው። ቃታ ሲስብ መኖሩን ረስቶታል። ሞንጆሪኖ ከአለቃዋ በተቃራኒ ዘናጭ ናት። አዲስ የወጡ **የአውሮፓ ፋሽኖች አያመልጧትም። የአይን መነፅሮቿ ሳይቀር በትዕዛዝ የሚሰሩ ናቸው።***

*ሞንጆሪና ከተስፋማርያም ቀጥላ ወደ ኢህአዴግ ቢሮ በመዘዋወር የካዛንችሱን መንግሥት ተቀላቀለች። የፕሮፓጋንዳ ዘርፉን እንድትመራ ተሰጣት። ከማዘጋጃ ቤት ማሚት የምትባል የትግል ጓዷ ተጨመረችላት። ማሚትና ሞንጆሪኖ የአዲስ አበባን **ፕሮፓጋንዳ በህወሃት የበረሃ ቅኝት አተራመሱት። በተለይም ዶንቦስኮ እየተባለ የሚጠራውን የካድሬ ማሰልጠኛ በበላይነት ተቆጣጠሩ።***

*የህወሃት መሰንጠቅ የሞንጆሪኖን ፍፁማዊ አገዛዝ እንዲያከትም አደረገው። አቶ መለስ እንዲህ አላት፣ "ሞንጆሪኖ አዲስ አበባን የለውጥ ማዕበል ውስጥ አስገብተሽ ታስተካክያለሽ ብለን ነበር የላክንሽ። አንቺ ግን የድርጅቱን አደራ በልተሽ ከጀርባ ስታርጂ ከረምሽ። ለመሆኑ ምን ጎድሎብሽ ነው? እነ ስዬን ሳታውቂያቸው ቀርተሽ ነው፣ አብረሽ ድርጅቱ ላይ ገመድ ልታጠልቂ የነበረው?"*

*ሞንጆሪኖ ተንሰቅስቃ አለቀሰች። ስጋ ስውአትን ጠርታ ሁለተኛ እንደማይለመዳት ቃል ገባች። እግሩ ላይ ተደፍታ ይቅርታ ጠየቀች። ከእነተወልደ ጋር እንዴት እንደተመሳጠረች ዘከዘከች።...አመናት። ፊቱን ወደ እሷ አነሳ...ራራላት።*

***እንደ ቀድሞ በሷ አባይ ፀሀዬ የምህረቱ ተቋዳሽ አደረጋት።** የዘመናዊ እውቀት ማነስ የፈጠረው ችግር ሊሆን እንደሚችል በመግለፅ የቀለም ትምህርት እንድትማር ፈረንጅ ሀገር ሰደዳት። ትምህርቷን አጠናቃ እንደመጣች ጓዟን ጠቅልላ መቀሌ ገባች። የትግራይን ካቢኔ ተቀላቀለች። ለአቶ መለስ ያላትን ታማኝነቷን በተግባር አሳየች።*

*እሱም ካሳውን በቁሙ ተቀበለ። በዚህ ሳይወሰን በህወሃት ሁለተኛ ትውልድ ውስጥ እንድትታቀፍ የመጀመሪያው ምርጫ አደረጋት።*

እነሆ መሀንዲስ መለስ አስቀድሞ በግምገማ ሞንጆሪኖን ቅስሟን ሰብሮ ገደላት። አቤቱ መለስ ሆይ ምህረትህን ስጠኝ! ብላ ተንሰቀሰቀች። አቶ መለስ ሞንጆሪኖ ከዘመናዊው ህወሃት መራሹ ዘመነ መሳፍንት ስውር መንግሥት ጋር ሆና ስለፈፀመቻቸው ሀገራዊ ወንጀሎችም ሆነ ስለዘረፈችው የህዝብ ሀብት ጉዳዩ አይደለም፤ እንደ ሌሎች ህወሃት/ኢህአዴጋውያን ዘራፊዎች ጓዶቹ ሁሉ። የሞንጆሪኖ ግፍና ዘረፋ ለአቶ መለስ እንደ መርሂ መንግሥትነቱ ወንጀል አይደለምና፤ አላስጠያቃትም። መለስን መካድና መልዕክተ ዜናዊን አለመቀበል ግን ለመለስ ከወንጀል ሁሉ ቀዳሚው ወንጀል ነበር። እናም የሞንጆሪኖ መለስን መካድ ወይም በመለስ ማመፅ ምክንያቱ የድንቁርና ውጤት ነው ብሎ ስላመነ ፊደል ለቀማ ሰደዳት። ለቅማ ስትጨርስ ሾማት። ረዥም እድሜ ለመለስ! እያለች የቀጣዩ ትውልድ አመራር አካል ሆነች! ገድሎ ማዳን…

ሞንጆሪኖ በቀድሞ ሥልጣን ዘመኗ በአዲስ አበባ ላይና በዶንቦስኮ የፈፀመቻቸው ጉደኛ ጉዶች በስፋት ተዘክዝከዋል - በመለስ ትሩፋቶች። አሁን ዘመን የቀድሞዋ ሞንጆሪኖ ስሟ *ፈትለወርቅ* ሆኗል። **ከአቶ መለስ ሞት በሁዋላ ሞንጆሪኖ/ፈትለወርቅ የህወሃት ማዕከላዊ ኮሚቴ አባል ሆናለች፤** መፅሀፈ ኤርምያስ እንደነገረን። እንግዲህ ሞንጆሪኖ በሀገራቱ ላይ ከሚወስኑት አካላት አንዷ ሆናለች። መለስ ሞተ እንጂ መንፈሱ አልሞተም…

**ክፍል ሶስት**

**የአብዮታዊ ዲሞክራቶች ምግባርና ሰብዕና፤ ለቅምሻ ለመነሻ፤**

ከ1983 ዓ/ም ጀምሮ በኢትዮጵያ መንበረ ሥልጣን ላይ የተቀመጠው ህወሃት መራሹ የኢህአዴግ መንግሥት መሪዎች የአብዮታዊ ዲሞክራሲ ፍጡራን ናቸው፤ አብዮታዊ ዲሞክራቶች። በዘመን ሂደት ደግሞ አብዮታዊ ዲሞክራሲ ይበልጥ እየተራቀቀ ሄዷል። አሁን ዘመን *'ልማታዊ መንግሥት'* የሚል ጭምብል አጥልቋል። በየዘመኑ ከሚፈለፈሉት የአዲሱ ትውልድ አብዮታዊ ዲሞክራሲ አራማጆች ጋር (ኤርምያስ ለገሰ የዚህ አዲሱ ትውልድ ምልምል ውጤት ነበር) ነባሮቹ ወይራ ህወሃታውያን/ኢህአዴጎች የሥልጣን ዘመናቸውን አልፋና ኦሜጋ ለማድረግ ሳይታክቱ ይሰራሉ። የሥልጣን አልፋና ኦሜጋ ባይኖርም በአብዮታዊ ዲሞክራሲ መርሆ ለእነሱ የሚሳናቸው ነገር ያለ አይመስላቸውምና!

የአብዮታዊ ዲሞክራሲና ልማታዊ መንግሥት አርኪቴክቱ አቶ መለስ ለሃያ አንድ ዓመት በዙፋኑ መንበሩ ኖሮ ቢያልፍም ዛሬም ድረስ በእነ በረከትና እሱን በተካው ሃይለማርያም ደሳለኝ በአጠቃላይ በህወሃት/ኢህአዴግ በፃዕረ መንፈስ ሀገራቱ ላይ ቀን ከሌት እንዳንዣበበባት አለ፤ በመለስ ራዕይ እንደተነገረን ከሆነ።

የመለስን ራዕይ ከግብ ለማድረስም ከአካለዊው ሞቱ ወዲህ አፈናው፣ እስሩ፣ ግድያውና ምዝበራው ተጠናክሮ ቀጥሏል። ስደቱ እንደ ጎርፍ ሆኗል። ትዕቢታቸው ከኢትዮጵያ አልፎ ሰንዓ የመን ድረስ ተጉዞ፤ ዓለም ዐቀፍ ህግ ገለመሌ ብሎ ነገር አናውቅም በማለት ተቃዋሚ ፖለቲከኛ የሆኑትን የግንቦት 7 ዋና ፀሀፊ አቶ አንዳርጋቸው ፅጌን አፍነው ወስደዋል። በዋሽንግተን ዲሲ የኢትዮጵያ ኤምባሲ ተቃውሞ ባደረጉ ሰላማዊ ኢትዮጵያውያን ላይ የጫካ ህጋቸውን ደንግገው ተኩስ ከፍተዋል። ህወሃት መራሹ ኢህአዴግ መረን ለቋል…

እነሆ በመፅሀፈ ኤርምያስ ላይ እኒህ አብዮታዊ ዲሞክራቶችን በየገፁ እናገኛቸዋለን። በሽበሽ ናቸው። መፅሀፉ የእነሱ ታሪክ ነውና። ለቅኝታችን

ያነጣጠርንባቸውን ጥቂቱን ለቅማሻ እናቀርባለን፤ ለሙሉ ማዕድ መፅሀፉ ኤርምያስን በአክብሮት እየጋበዝን።

**ከዚያ በፊት ግን፤**

*******************

*“አዲስ አበባዬ፤ ጠላት ያወደማት የጥንታዊ ከተማ ፍርስራሽ የመሰሉ ቤሳ ገላዎቿ አልፎ አልፎ ይታያሉ። እነዚህ የነውር ስራዎች ተመሳሳይ ገመና መሸፈኛ የብረት ሸርጥ አገልድመዋል። ቢጫና አረንጓዴዎቹ የብረት ሸርጦች ከሩቅ ሲያዩዋቸው ልምላሜ እንዲመስሉ የታቀዱ የውድመት መጋረጃዎች ናቸው። ከበስተጀርባው ብዙ ህይወት፤ ብዙ ኑሮ ዳዋ ውጦ ይታየኛል። የብረት አጥሮቹ ግን ይሄን የመቃብር ጩኸት በደማቅ ቀለሞቻቸው ለመዋጥ ትንቅንቅ ገጥመዋል። መንግሥት በዶሮ ስልት ለመጫር ተፈጥሮው ሲል ብቻ የመነቃቀራቸው ገመናዎቹ በእነዚህ የብረት ዘቦቹ ተከበዋል። የታጬት መሬቶች ሳይዳኑ ቆመው ቀርተው መንግሥት ጠለፋውን ጋብ ለማድረግ እንኳን ፈቃደኝነት አላሳየም። ከተፈናቀሉት የታነቁት፤ ከታነቁት ደግሞ የተዛተባቸው ይበልጣሉ። መንግሥት በእጁም በእግሩም የከተማ አጨዳ ላይ ተሰማርቷል። መሬትን እንደ መክሊት ቆፍሮ መቅበርን ሥራዬ ብሎ ተያይዞታል። ወይ ከተማዬ!”*

*ዓለማየሁ ገላጋይ፤ ‘ኢህአዴግን እከስሳለሁ’ (2004 ዓ/ም)*

**********************

*“ምርኮ ፈጠነ፤ ብዝበዛ ቸኮለ” (ትንቢተ ኢሳይያስ ምዕ. 8. ቁ.1)*

***********************

አሁን ወደ አብዮታዊ ዲሞክራቶች ምግባርና ሰብዕና እንገባለን።

**1. ‘ንጉሥ’ ተስፋማርያም - መንግሥቲ ዘካዛንችስ**

መልዕክተ ኤርምያስ እንዲህ ተላልፏል፤

*የካዛንችሱ መንግሥት በሶስት የህወሃት ካድሬዎች ይመራ ነበር። ተስፋማርያም ሞንጆሪኖ እና ፍሰሃ መአሲ። በአጃቢነት ደሳለኝ ሸሹ፤ ሊሻንና ዮሀንስ የሚባሉ የብአዴን ካድሬዎች ተመድበዋል። ተስፋማርያም የበላይ ሹም ነበር። **ህዝቡ ሳይሆን እነ ተወልደና ስዩ የቀቡት።** ነዋሪው የት አይቶት? የት አውቆት?*

*ተስፋማርያም የቀደምት የህወሃት ታጋይ ነበር። በብረት ትግሉ ወቅት በፖለቲካ ዘርፍ ተመድቦ ህዝብ አደራጅቷል። **ከደርግ ውድቀት በሁዋላ  አዲስ አበባ ተሰጠችው። እንደግል ንብረቱ ቆጠራት።** ለከተማዋ ካድሬ ይመድባል። ያባርራል። ያስራል፤ ይፈታል። መሬት ይሰጣል፤ ይቀማል። ግብር ይጨምራል፤ ምህረት ያደርጋል። ለከተማዋ በጀት ይደለድላል፤ ይቀንሳል። መስጊድና ቤተ ክርስቲያን እንዲሰራ ይፈቅዳል፤ ያስፈርሳል። ታዲያ ይህን ሁሉ የሚያደርገው በስውር ነበር። ከከተማ ካድሬዎች በአካል የምናውቀው ጥቂቶች ነበርን። ብዙሃኑ አይቶት አያውቅም። በስሙ ብቻ ይርድለታል።*

*በድሮ ጊዜ “ንጉሡ ምን አሉ” ተብሎ እንደሚጠየቀው ሁሉ እኛም የተስፋማርያምን ትዕዛዝ ለመስማት እናነፈንፋለን። ትዕዛዙ የንጉሥ ነበር። በተባለው ቀን የሚፈፀም።*

*ባህታዊው አራት ኪሎ እነ ተወልደ ወልደማርያም ጋር በመሄድ መመሪያ ይቀበላል። ከዛ ውጪ ከካዛንችስ አይወጣም። እሱና ተወልደ በብዙ ነገር ይመሳሰላሉ። የጋራ ባህርይ አላቸው። ላባቸው አንድ የሆነ ወፎች! አመራር ባህሪያቸው ተመሳሳይ ነበር። በእነሱ ዘመን የመንግሥት ተቋማት የሥራ ትዕዛዝ የሚወስዱት ከፓርቲው ፅ/ቤት*

*ነበር። እቅድ ኢህአዴግ ቢሮ በእነ ተወልደ ተዘጋጅቶ በመመሪያ መልኩ ለእነ መለስ ይወርዳል። የዕዝ ሰንሰለቱ ከድርጅት ወደ መንግሥት ይፈሳል።*

*በዚህ መሰረት ተወልደ መለስን፣ ሰለሞን ጢሞ ኩማ ደመቅሳን፣ ቢተው በላይ አባተ ኪሾን፣ ተስፋማርያም ደግሞ አሊ አብዶን የሥራ መመሪያ ይሰጣሉ።*

ይህ ቅንጭብ ታሪክ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ አንድ የታሪክ ምዕራፍ ያስታውሰናል፤ ዘመነ መሳፍንትን! ታሪክ ራሱን ይደግማል? የት ነው ያለነው? ዘመኑስ ስንት ነው? እነሆ ዘመናዊ ዘመነ መሳፍንት በዘመነ ህወሃት/ኢህአዴግ። አራት ኪሎ ሁለት መንግሥታት ይገኛሉ። ለጊዜው ያደባው በ'አፄ' መለስ የሚመራው መንግሥትና በመንግስቱ ውስጥ እየገነነ የመጣው ሌላው የመሳፍንቱ የእነ ተወልደና ስዬ መንግሥት። እንግዲህ ባህታዊው 'ድንቄም ባህታዊ' የአዲስ አበባ ገዢ ነው፤ በስሩ ደግሞ እብዱ አሊ አብዶ፣ የአዲስ አበባ ፕሬዚዳንት አለለት።

እነሆ እነዚህ ሁለቱ በመመሪያ ቁጥር አንድ አዲስ አበባን ጋጡዋት፤ ተስፋማርያም የአባቱ እርሻ አደረጋት፤ ቸበቸባት፤ ባጥንቷ አስቀራት፤ የኢትዮጵያን መዲና። የዘመነ መሳፍንት ፍጥጫና ፍትጊያ ሲፈነዳ አሸናፊው ትንንሾቹ ነገሥታት ሳይሆኑ 'አፄ' መለስ ሆነ። የአዲስ አበባ ወረራም ናረ፤ እንደ ሮኬትም ተወነጨፈ። *አዲስ አበባን እንደ መክሊት ቆፍረው ቀበሯት፣ መዘበሯት።* መፅሀፈ ኤርምያስ በአዲስ አበባ ላይ ያለማባራት ስለወረደው ምዝበራና ጭካኔ፤ ቂምበቀልና ወረራ በስፋት ዶሴውን ይፋ አውጥቷል፤ ከፕሬዚዳንት አሊ አብዶ አስከ ከንቲባ አርከበ ዕቁባይና ከንቲባ ኩማ ደመቅሳ ዘመን ድረስ። አንድ ቀን አዲስ አበባ ራሷ ትፋረዳቸዋለች። ይህን አዘግይተን ወደተነሳንበት የተስፋማርያም ታሪክ እንመለስ።

*መፅሀፈ ኤርምያስ በጨፌው ግምገማ ወቅት ስለሆነው እንዲህ አንጥቧል፤*

*የህወሃት መሰንጠቅ የተስፋማርያምን አገዛዝ እንዲያከትም አደረገው። ትልቁ ዛፍ ወደቀ። ተስፋማርያም ከህወሃት መሰንጠቅ በሁዋላ የአሊጋ ቁራኛ ሆኗል። (ወደ ጨፌው ግምገማ) እንዲመጣ የተወሰነበት በዚህ ሁኔታ ላይ እንዳለ ነበር። ተስፋማርያም በፍሰሃ ተደግፎ ወደ አዳራሹ ገባ።...*

*ተስፋማርያም በቁሙ አልቋል። የጉንጮቹ አጥንቶች ቆዳውን በስተው ሊወጡ ይታገላሉ። ፀጉሩ ተኗል። ሲጉረጠረጡ የሚያስፈሩት አይኖቹ ተደብቀዋል። እጆቹ ከመሰለላቸው የተነሳ ከዘራው ከብዷቸዋል። የምግብ ጉዳት እንዳጋጠመው ሰውነቱ ይመሰክራል። አፈር፣ አፈር ይሸታል። መልአከ ሞት ቀርቦታል!*

እነሆ የዘመናዊው ዘመነ መሳፍንት ንዑስ "ንጉሥ" ተስፋማርያም ወድቋል። መልዕክተ ዜናዊን የተፃረሩ የራሱ ውልዶችም ቢሆኑ እንኳን ህወሃት እንደ ድመት የራሱንም ፍጡራን ይቀረጭጫልና። እነ ስዬም ወድቀዋል፤ 'አፄ' መለስ ቢያደባም የዋዛ አልነበረምና። በእኛ በኩል ባህታዊውን 'አፈር ይቅለለው' አንልም!

የህወሃት/ኢህአዴግ የግምገማ መድረክ የዜሮ ድምር ገበጣ መጫወቻ መድረክ ነው፤ ድርጅቱን ለማዳን መግደያ። በዚህ መድረክ 'አብዮታዊ ዲሞክራሲን' ተጋፍቶ ለተገኘ ወዮለት፤ እንደ ተስፋማርያም በአፅሙም ቢሆን ተጎትቶ ይቀርባል። ተጋዳሊቶችና ተጋዳዮች ታዳምያን በፍርሃት ይርዳሉ፤ 'ነግ በኔ' መሆኑን እያስተዋሉ፤ ተስፋማርያምን ያየህ ተቀጣ ይላሉ...

## 2. አወይ መርካቶ፤ አወይ ጉራጌ!

ተከታዩ ታሪክ የተፈፀመው ከዘመነ መሳፍንት ማክተም በኋላ ነው፤ የአብዮታዊ ዲሞክራሲ መሀንዲስ የአቶ መለስ ሙሉ መዳፍ በመላው ኢትዮጵያ ላይ ከተጫነ

በኋላ። የህወሃት መራሹ ኢህአዴግ ቁጣ አዲስ አበባ ላይ ይበለጥ የተንቀለቀለበት ዘመን፤ አዲስ አበባ በቀን ጅቦች የተጋጠችበት ዘመን። ለአብነት የምናቀርባት የዚህ ወቅት ተምሳሌተ ፍጡር፤ ሮማን ትባላለች፤ ታሪኩን 'ለማመጣጠን'። 'ገድለ ሮማን' በመልዕክተ ኤርምያስ እንዲህ ተፅፏል፤

በአፍሪካ ትልቋ ገበያ የሆነችውን ውስብስቧን መርካቶን (ለ)መምራት አርከበ ከትግራይ ሮማን ተስፋዬ የምትባል ካድሬ አምጥቶ ስራ አስኪያጅ አድርጎ ሾማት። ሮማን ወፍ ከሰማይ የምታረግፍ፤ በንግግሯ አራት ነጥብ የማታውቅ የመቀሌ ጩልሌ ናት።

ሮማን አዲስ ከተማን ነገሰችበት። መርካቶን አሳርሳ ለአዲሶቹ የህወሃት ባለሀብቶች ቸበቸበች። አርከበ ከባላንጣዎቹ እነ ተወልደና አለምሰገድ ተረክቦ ያስቀጠለውን የህወሃት ባለሀብቶች መፍጠር አላማ ዋነኛ አስፈፃሚ ሆነች። የጉራጌ ነጋዴዎችን ደም እምባ አስለቀሰች። የህወሃት ነጋዴዎችን የመፍጠር ስትራቴጂ እዛው ሳለ የጉራጌ ነጋዴዎችንና ባለሀብቶችን ማዳከም የሚል አላማ እንደነበረው ተደጋግሞ ተገልጿል። ኢኮኖሚውን የሚቆጣጠር ሀይል በሂደት ፖለቲካል ኢኮኖሚው ላይ የበላይነት ማሳረፉ ስለማይቀር ጉራጌን ከንግዱ ዓለም ማስወጣት ለጥያቄ የሚቀርብ አይደለም። ሮማን የጉራጌ ነጋዴዎችን እንዳያንሰራሩ የምትቀጣበት ምክንያት ይህ ነበር።

እነ ሮማን በፈጠሩት ልዩነት ጉራማይሌዋ መርካቶ ይበልጥ ተዘበራረቀች። ተመሳሳይ እቃዎች በአዲሶቹና ነባር ነጋዴዎች መካከል የዋጋ ልዩነት አሳየ። የግብርና ሊዝ እፎይታ ያገኙት አዲሶቹ ነጋዴዎች ዋጋቸውን አወረዱ። ሸማቹ ምሥጢሩ ሳይገባው ቅናሽ ወዳገኘበት አዲሶቹ ነጋዴዎች ፊቱን አዞረ። ቀስ በቀስ ነባሩ ነጋዴ ከገበያ ወጣ።

የማፍያ ባህሪ ያላቸው አዲሶቹ ነጋዴዎች ሰው ሰራሽ እጥረት በማስከተልም ተወዳዳሪ አልነበራቸውም። በሰአታት ውስጥ የአንድ ኪሎ ጨው ዋጋ ከአንድ ብር 50 ብር የተሸጠበትን አጋጣሚ ልብ ይሏል።

ሉሌና ሮማን ከቢሯቸው ሳይወጡ ከአስር እጥፍ በላይ ግብር እንዲጥሉ ሙያተኞቹን አስገደዱ። ከስረው ለመዝጋት አፋፍ ላይ ያሉ ነጋዴዎችን ከግብር ህጉ በተቃራኒ ታክስ አስከፈሉ። በድርጊቱ የተበሳጨ አንድ ነጋዴ ራሱን በገመድ አንጠለጠለ። ተመሳሳይ ሱቅና የንግድ አይነት ያላቸውን ጎረቤት ነጋዴዎች አንዱን በዜሮ፤ ሌላውን በአስር ሺዎች ታክስ እንዲከፍል አድርገዋል። ይህ በዘር ላይ የተመሰረተ እርምጃ ቀድሞ በነጋዴዎች ዘንድ የነበረን መደጋገፍ እንዲቀር በማድረግ እርስ በርስ በጥላቻ እንዲተያዩ አድርጓል። በዚህ ምክንያት መሳሪያ የተማዘዙ፤ በገጀራ ተፈነካክተው ወህኒ የወረዱ ነጋዴዎች ይገኙበታ።

ይህ የ'ገድለ' ሮማን ታሪክ የህወሃት መራሹ ኢህአዴግ አዲሲቷ ኢትዮጵያ ታሪክ ነው። አብዮታዊ ዲሞክራሲ የወለደው ልማታዊ መንግሥት ታሪክ። ይጎመዝዛል፤ ያጥወለውላል። እንደምን ያለ መንግሥት ቢሆን ነው ራሱ በሚመራው ህዝብ ላይ እንዲህ ያለ ጭካኔን ያለመታከት፤ ያለመሰልቸት ሳያሰልስ ቀን ከሌት እያሴረ የሚፈፅመው? እኔስ አብዮታዊ ዲሞክራሲን መግለፅ አቃተኝ….

ለመሆኑ ሮማን የት ደረሰች? ብለን እንጠይቅ። መፅሀፉ ኤርምያስ እንደነገረን ከሆነ የነሮማንን የመርካቶ ንግሥና ምርጫ 97 አደናቀፈባቸው ብሏል። የጠገቡ ጅቦች ሂደው ሌሎች ያልበሉ ጅቦች ተተኩ። ሮማንም የጡት አባቷን አርከበ እቁባይን ተከትላ ወደ ከተማና ልማት ተዘዋወረች - በማለት ተፅፏል በመልእክተ ኤርምያስ። እነ ሮማንና አርከበ ከተማ ሊያለሙ። ሮማን ወንጀለኛ ነች። ሉሌ ወንጀለኛ ነው። አለቃቸው አርከበ ወንጀለኛ ነው። የዘረፉትን አፍንጫቸውን ተሰንገው መልሰው ስለፈፀሙት ግፍና ምዝበራ ደግሞም በእነሱ ኢፍትሃዊ ታክስና ሊዝ ህይወታቸው ስለጠፋ ነጋዴዎችም

ፍትህ ሲባል በእግረ ሙቅ ታስረው (እነሱ ሌሎችን እንደሚያደርጉት) ቃሊቲ መውረድ የነበረባቸው ወንጀለኞች። ግና 'አባቱ ዳኛ፤ ልጁ ቀማኛ' ሆነና በልማታዊው መንግሥት ዜሮ ድምር ጨዋታ፤ ከተማ ልማት ገቡ... ድንቄም ልማት!!

## 3. የኮሪኔሎቹ ድራማ

እውነት፤ እውነት እላችኋለሁ - የኮሪኔሎቹን ድራማ ከኤርምያስ ውጪ ሌላ ደራሲ ፅፎት ባነበው ምናባዊ የሆነ ግሩም ድርሰት እንጂ በገሀዱ ዓለም በዕውን የተፈፀመ *የህወሃት መራሹ ኢህአዴግ መንግሥት ታሪክ ቁንፅል አካል ነው ብዬ ከቶም አላምንም* ነበር። የልቤን ነው የነገርኳችሁ - ቃል ለምድር ለሰማይ!

ካላመናችሁኝ አንብባችሁ ፍረዱ! መልዕክተ ኤርምያስን እማኝ አቀርባለሁ፤ እንዲህ ይነግራችኋልና፤

*በምርጫ 97 ማግስት በዋለ አንዲት ጠዋት ሶስት ሄሊኮፕተሮች ተከታትለው በአሮጌው አውሮፕላን ማረፊያ ሜዳ ላይ አረፉ። የአካባቢው ነዋሪ የኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት የተቀሰቀሰ መስሎት በሀዘን ተዋጠ። እኛ ካድሬዎች ደግሞ አቶ መለስ ያቋቋመውን ሰባት ማዘዣ ጣቢያ ለማጠናከር የመደባቸው ተጨማሪ ወታደራዊ መኮንኖች እንደሆኑ ጠረጠርን። እኛም ሆነ ነዋሪው የገመትነው ልክ አልነበረም።*

*ከሄሊኮፕተሮ ውስጥ የወጡት ስምንት የኮሪኔል ማዕረግ የለበሱ ወታደሮች ነበሩ። መኮንኖቹ በቀጥታ ፊት ለፊታቸው ወደሚገኘው የኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ሄዱ። የከንቲባ አባተ ስጦታው ቢሮ። መሬት እንደሚሰጥ መረጃ ደርሷቸው ከጦር ግንባር እንደመጡ ነገሩት። እያንዳንዳቸው የማህበር ስም የተሰጣቸው የአስራ ሁለት መኮንኖች ስም ዝርዝርና ፊርማ የያዘ ወረቀት አስረከቡት። "ዘመቻ ፀሀይ ግባት የቤት ማህበር፤ ሀየሎም አርአያ የቤት ማህበር፤ ዛላአንበሳ ቤት ማህበር፤..."*

*አባተ ደነገጠ። የተሰጠው መመሪያ ስለሌለ እንደማይፈርም ተናገረ። መንግሥታዊ አሰራርን አስረድቶ ሳይጨርስ ግንባሩ ላይ ከተደቀነ ሽጉጥ ጋር ተጋፈጠ። ማስፈራሪያዎች ተዥጎደጎዱ። "የቅንጅት ተላላኪ መሆንህን ደርሰንበታል፤ ኢህአዴግ እንዲሸነፍ ያደረጋችሁት እንዳተ ያሉ ሰርጎ ገቦች ናቸው፤...*

*በዚህ አስጨናቂ ሰአት ነበር ምክትል ከንቲባው ነጋ በርሄ የአባተን ቢሮ በርግዶ የገባው። አባተ ላይ ከተነጣጠረው ሽጉጥ አንዱ ወደሱ ዞረ። ነጋ የዶሮ ላባ የተደቀነበት እንኳን አልመሰለውም። መሳደብ ጀመረ፤ ነፍጥ ከእናንተ በፊት አንግበን ተራራ ደርምሰናል። የምታስፈራሩትን ሂዱና ሌላ ቦታ አስፈራሩ፤ ይላቸዋል። ተደናግጠው መሳሪያዎቻቸውን ወደ አፎታቸው ይመልሳሉ። ሙልጭ አድርጎ ከሰደባቸው በሁዋላ ከንቲባውን ይቅርታ እንዲጠይቁ ያዛቸዋል። በተባሉት መሰረት ወታደራዊ ይቅርታ ጠየቁ። ነጋ የመጨረሻውን ተግሳፅ ተናገረ፤*

*'ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ ጥያቄያችሁን ብታቀርቡ ኖሮ አባተ እንኳን ቤተሰባችሁን ጥላችሁ ግንባራችሁን ለጥይት ለምትሰጡት ቀርቶ ለሌላውም አይጨክንም። ያውም ከቀናት በሁዋላ ጠላት ተረክቦ ለሚዘርፋት አዲስ አበባ!' አባተ መሬቱን ፈቀደ።*

*መኮንኖቹ የተሰጣቸውን መሬት እንኳን ማየት አልፈለጉም። እያንዳንዳቸው ከግማሽ ሚሊዮን ብር አየር ባየር ተቀበሉ። ኮሪኔሎቹ ሌሊቱን ሙሉ ከበርሃ ትግል ጓዳቸው ነጋ በርሄ ጋር የጥንቱን እያወጉና እየጨፈሩ አሳለፉ። ወፍ ሳይንጫጫ አመስግነውት ወደ ግንባር ተመለሱ።*

*ነጋ ተልዕኮውን በማጠናቀቁ በብርሃን ፍጥነት መቀሌ ተላከ። የህወሃት ማዕከላዊ ኮሚቴና የትግራይ ክልል ካቢኔ ውስጥ ተቀላቀለ...ዘመን አለፈና አዲሱ ለገሰን ለማገዝ ኢህአዴግ ቢሮ (አአ) የሥልጠና ማዕከል በምክትል ሚኒስትርነት ማዕረግ ተመደበ።*

ይህ አስደማሚ፤ አስደንጋጭና ዘግናኝ ድራማ በውስጡ አያሌ ግዙፍ ሀሳቦችን ይዟል። በዝርዝር ማብራራት አንሻም፤ አንባቢ ይብከንከንበት። ኢትዮጵያ ያለችበትን ፀለምት ዘመን ያብሰልስልበት...ነገር ግን፤

ህወሃቱ ነጋ በርሄ ወንጀለኛ ነው። ዘራፊ፤ አስዘራፊ። የህወሃት ኮረኔሎች ወንጀለኞች ናቸው። ዘራፊዎች፤ እንደ ወንበዴ። የጠላት ሀገር እንኳን እንዲህ ተደርጎ አይዘረፍም። በአስራሁለት ኮረኔሎች ስም እያንዳንዳቸው ከግማሽ ሚሊዮን ብር በላይ በድምሩ አየር ባየር ከስድስት ሚሊዮን ብር በላይ ዘርፈውና ሌሊቱን በውስኪ ጨብ ብለው ወፍ ሳይንጫጫ እንደ ወንበዴ ወደ ጫካቸው፤ ወደ መቀሌ። ነጋም ተከትሎ ጫካ፤ መቀሌው ገባ። ስለ ‘አስደናቂ’ ድራማው የህወሃት ከፍተኛው የሥልጣን እርከን ተሰጠው፤ የማዕከላዊ ኮሚቴ አባል። ሰንባብቶ ደግሞ ወደ አዲስ አበባ ተጠራ፤ እነሆ በወዲ ዜናዊ ቡራኬ ነጋ በርሄ ዳግም ነጋለት፤ ሚኒስትር ሆነ...ነጋም ሆነ ኮረኔሎቹ፤ ሁሉም ለፍርድ ቀርበው መቀመቅ መውረድ ነበረባቸው፤ እንጂ ሹመትና ሽልማት አልነበረም ምሳቸው። ግና አስቀድሞ እንደተባለው፤ ‘አባቱ ዳኛ ልጁ ቀማኛ፤ ልማታዊ መንግሥት ጠበቃ!’ ሆነና ዘርፎ ያስዘርፉል። ለመሆኑ እንዲህ ያለውን ዘረፋ አርኪቴክቱ አያውቅም የሚሉ ይኖሩ ይሆን፤ የመለስ ራዕይ ደቀ መዝሙራን? ወዲ ዜናዊ አዲስ አበባን በመልዕክተ ዜናዊ አዋጅ ሲያዘርፍ፤ እንዲህ ነበር ያደረገው፤ መፅሀፈ ኤርምያስን እናቀርባለን፤

*የምርጫ 97 ውጤት እንደታወቀ አቶ መለስ ከመከላከያ ጄኔራሎች ጋር በየቀኑ ስብሰባ ይቀመጣል። የፀጥታና ወታደራዊ ሃይሉን ማጠናከር፤ ፖለቲካዊ ጤንነቱን መጠበቅ። እናም የወታደራዊ ሃይሉን ወገንተኛነት የሚያረጋግጥበት ሁኔታ መፍጠር ነበረበት። ጄኔራሎቹም ይህንን ጠንቅቀው ያውቃሉ። ጄኔራሎቹ በቀኝ እጃቸው የታማኝነት ማህተም፤ በግራ እጃቸው ደግሞ ማመልከቻ ይዘው መጡ። ማመልከቻው አዲስ አበባ በቅንጅት እጅ ከመውደቋ በፊት በቋሚነት ጎናችንን የምናሳርፍበት መሬት (ቦሌ ክፍለ ከተማን) ይሰጠን የሚል ነበር።*

*አቶ መለስ ሳያቅማማ ጥያቄያቸውን በመቀበል ለከተማው ከንቲባ አርከበ እቁባይ ትዕዛዝ ይሰጣል። መመዘኛው ደግሞ ከ1978 ዓ/ም በፊት በትግል ውስጥ የነበሩና ማዕረጋቸው ከኮረኔል በላይ እንዲሆኑ ይነግረዋል። ከሙሉ ኮረኔል በታች ያሉት ወታደሮች በሌሎች ማስፋፊያ ክፍለ ከተሞች ተመደቡ። ወሬው ባድመና ፆረና ጦር ግንባር ድረስ ተዳረሰ። ወታደራዊ መኮንኖቹ ምሽጋቸውን እየለቀቁ በጦር ኢሊኮፕተር ጭምር እየተሳፈሩ አዲስ አበባን ወረሯት። ይህንን ተከትሎ የከተማው መሬት ሙሉ ለሙሉ በሚባል መልኩ ተሰረቀ። ከቀናት በሁዋላ አዲስ አበባ አጥንቷ ተግጦ እርቃኗን ታየች። አዱ ገነትና ልጆቿ አለቀሱ...*

ወዲ ዜናዊ ማለት እንግዲህ እንዲህ ያለ ጨካኝ፤ እንዲህ ያለ እኔ ከሞትኩ ሀገር አትኑር ባይ፤ እንዲህ ያለ ዘረኛ፤ እንዲህ ያለ የክፋት ሁሉ ቁንጮ የነበረ መሪ ሆኖ ቆይቷል። የሚያስተዳድራትን ሀገር መዲና አስዘርፏል። አቶ መለስ የዘረኝነት እሾህ አክሊል ያጠለቀ ዘረኛ መሪ ስለመሆኑ ከክምር መረጃዎች አንድ ሰበዝ መዝዘን ለአባባላችን ማጠናከሪያ ከመልዕክተ ኤርምያስ እናክላለን፤

*በአቶ መለስ የፍራቻ ቻርተር መሰረት አዲስ አበባ በአስር ክፍለ ከተማ የተከፈለች ሲሆን የአራቱ ክፍለ ከተማ ከንቲባዎች አርከበ ከትግራይ ይዟቸው የመጣው የህወሃት ካድሬዎች ነበሩ። ቂርቆስን አተይ (በአሁኑ ሰዓት የኤፈርት ማርኬቲንግ ዳይሬክተር)፤ የካ ግርማፅዮን (በአሁኑ ሰዓት የአፋር ጋምቤላ ቤንሻንጉል፤ ሱማሌ የበላይ ጠባቂ)፤ ላፍቶ ሀይሌ ፍሰሃ (በአሁኑ ሰዓት የአዲስ አበባ ሥራ አስኪያጅ)፤ ቦሌ ሀብተ ሥላሴ (የትግራይ ዞን አስተዳዳሪ)። ከንቲባ ባልሆኑባቸው ክፍለ ከተሞች ደግሞ ምክትል ነበሩ።*

(በድምሩ በሰባት ክፍለ ከተሞች ህወሃት ከንቲባና ምክትል ከንቲባነቱን ወስዷል። በተቀሩትም አዛዥና ናዛዡ ህወሃት ነው።)

*የመልዕክተ ኤርምያስ ዶሴ እንደገላለጠው፣ በድዱ ያለው ፀረ ሙስና ኮሚሽን በድዱ አጥንቶ ባቀረበው ሪፖርት እስከ 2003 ዓ/ም (ወዲ ዜናዊ ገና አለማለፉን ልብ ይሏል) ከ3.5 ሚሊዮን ካሬ ሜትር የሚደርስ የአዲስ አበባ መሬት በወረራ ተዘርፏል። ይህ በገንዘብ ሲሰላ ከአስር ቢሊዮን ብር በላይ በህወሃት መራሹ መንግሥት ከህዝብ ተዘርፏል።* በድዱ የሚኖረው ኮሚሽን ያቀረበው ውስጣዊ ሪፖርት የመከላከያውና የኢህአዴግ ተቋማት የዘረፉትን አያጠቃልልም፣ *መፅሀፈ ኤርምያስ እንዳሳወቀው።*

እነሆ የመለስ ራዕይ እስከዚህ ደረጃ የወረደ ቃላት በትክክል ሊገልፁት የማይችሉት ርኩስ ራዕይ ነው! መለስ ወንጀለኛ መሪ ነበር!! ህዝባዊ ወያኔ ሃርነት ትግራይ ወንጀለኛ ድርጅት ነው። የኢህአዴግ መንግሥት ወንጀለኛ መንግሥት ነው። ህወሃት እንደ ድርጅት ብቻ ሳይሆን በውስጡ የታቀፉት አባላቱም ጭምር ከትግራይ ክልል ውጪ የምትገኘዋን ኢትዮጵያ የጠላት ሀገር ናት ብለው የሚያምኑ ብቻ ሳይሆን በዚህች የጠላት ሀገር ለሚፈፅሙት ዝርፊያና ወንጀል የሞራል ተግሳፅ እንኳን የሚሰማቸው አይደሉም። ይህ ጥቅል አቋም የተሳሳተ ወይም አለቅጥ የተለጠጠ ነው ብሎ ለሚያስብ ደግሞ፣ 'ማን ያርዳ የቀበረ፣ ማን ይናገር የነበረ' እንዲል የአበው ንጥረ ቃል፣ የመለስ 'ትሩፋቶች'ን ምሥክርነት እናቀርባለን። የሚከተለውን ልብ ይሏል፣

*የህወሃት ካድሬ የእነ ስዬን ንቅዘት እያወቀና በዓይኑ በብረቱ እያየ አላጋነነውም። የህወሃት ካድሬዎች ዘንድ ሌብነትን በተመለከተ አደገኛ አመለካከትና አዝማሚያ እንዳለ (አቶ መለስ) ያውቃል። የህወሃት አባላት በትግራይ ክልል ሙስና ከሞላ ጎደል በቁጥጥር ስር ውሏል፣ ሌብነት የሥርዐቱ አደጋ አይደለም ብለው ያምናሉ። በሌላ በኩል ፌዴራልና አዲስ አበባ ተመድቦ የሚሰራ የህወሃት ካድሬ ሰረቀ ሲባል አይጋነንም። በእነዚህ ተቋማትና አዲስ አበባ መመደብ ሎተሪ እንደደረሰው ይነገራል። "እንኳን ደስ አለህ" ይባላል። ዘርፈው ሲገኙም እንደሌላው ባለሥልጣን ድርሻቸውን እንደወሰዱ ይቆጠራል። ብዙዎቹ ከፌዴራልና አዲስ አበባ በዘረፉት ገንዘብ መቀሌ ላይ አፍ የሚያስከፍቱ ቪላዎችን ገንብተዋል። በተለይም በአካል ተገኝቼ ያየሁዋቸው ሐውልቲና ገረብ የሚባሉት አካባቢዎች የምዕራቡ ዓለምን ህንፃዎች የሚያስንቁ ናቸው።*

## ክፍል አራት

### ውጤት አልባዎቹ ሕዝብዊ ሠላማዊ 'አብዮቶች'

ለመነሻ፣

በቅኝታችን መጀመሪያ ገፆች - *'የመለስ ትሩፋቶች'፣ ባለቤት አልባ ከተማ* - ታሪክ የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ አካል ነው ማለታችንን ያስታውሷል። ጥቂት መስመሮችን እናክልበት። በጥቅምት ወር 1995 ዓ/ም ቦሌ መንገድ በሚገኘው የኦሮምያ ምክር ቤት (ጨፌ) በተካሄደው ጉንጭ አልፋ ግምገማ (መፅሀፈ ኤርምያስ እንደሚጠራው) የሚጀምረው መልዕክተ ኤርምያስ እስከ መፅሀፉ መገባደጃ በሶስት የታሪክ ምሶሶዎች ላይ ወደፊትና ወደ ሁዋላ በመመላለስ ያጠነጠነ ነው። ምርጫ 92፣ ምርጫ 97 እና ምርጫ 2000 ዓ/ም። ከውስጥ ወደ ውጪ የተነገረ ታሪክ። በጥልቀት በስፋትና በመረጃዎች የታጀበ ታሪክ። ስለ ምርጫ 97 አያሌ መዛግብት በፅሁፍ ለንባብ ቀርበዋል። ብዙ እጅግ ብዙ ተነግሯል። በመፅሀፈ ኤርምያስ ከውስጥ ወደ ውጪ የቀረበው ታሪክ ደግሞ የወቅቱ የኢትዮጵያ ህዝብ የትግል ታሪክ በህወሃት መራሹ ኢህአዴግ ጎራ ያስከተለውን አንድምታ ሲተርክ እጅግ ያስደምማል።

ይሁንና ከምርጫ 97 በፊት ምርጫ 92 ተካሂዶ ነበር። ስለዚህ ምርጫ ታሪክ ማንም የነገረን የለም። ከውጪ ወደ ውስጥ ወይም ከውስጥ ወደ ውጪ። መሪም ሆነ አይዞህ ባይ

ያልነበረው ሕዝብ ብቻውን ታግሎ ብቻውን የተሸነፈበት ታላቅ ታሪክ። “ኢህአዴግን ከአዲስ አበባ ያባረረው ምርጫ” ይለዋል መልዕክተ ኤርምያስ። ታሪኩን ደግሞ “የተዳፈነ ታሪክ” ሲል በሰፊው ዘክሮታል። በ97 ምርጫ የተቀናጁትና ሕዝቡ ከጎናቸው እንደ ችቦ የቆመው መሪዎች በ92 ዓ/ም ግን አልነበሩም። *በወቅቱ (በ1992 ዓ/ም) ሥርዐቱን ለመጣል በሕዝቡ ውስጥ የነበረው አቋምና የመሪና የድርጅት ማጣት ሥርዐቱን በተመለከተ በሕዝብና በመሪዎች መካከል የግንዛቤ ቅደም ተከተል ኖሮ ይሆን? ያስብላል። ሕዝብ ቀድሞ የሥርዐቱን ንቅዘት ተገንዝቦ - መሪ ዘግይቶ የተከተለበት?*

ሶስተኛው ታሪክ የተከወነው በሚለንየሙ ወቅት ነበር፤ በምርጫ 2000 ዓ/ም። **ለሁለተኛ ጊዜ ብቸኛው ሕዝብ ከህወሃት መራሹ ኢህአዴግ ጋር ብቻውን የተናነቀበትና ጥሎ የወደቀበት ምርጫ።**

እነሆ እንግዲህ በዚህ ቅኝት እኒህን ውጤት አልባዎች ሶስት ሕዝባዊ ሠላማዊ አብዮቶች ወፍ በረር ዳሰሳ እናደርግባቸዋለን።

## ምርጫ 1992 ዓ/ም

እነሆ በመለስ ትሩፋቶች መልዕክተ ኤርምያስ እንዲህ ተላልፏል፤

*ብዙዎች የአዲስ አበባ ህዝብ ምርጫ ካርድ በምትባል ሠላማዊ ወረቀት ኢህአዴግን የቀጣው በምርጫ 97 አድርገው ይቆጥራሉ። ይህ የተሳሳተ ነው። **ኢህአዴግ ላይ የመዲናይቱ ህዝብ የወሰነው በሁለተኛው ሀገር አቀፍ ምርጫ 1992 ዓ/ም ነበር። በዚህ ምርጫ ኢህአዴግ አሳፋሪ ሽንፈት ተከናንቧል።** ይህ ብዙ ያልተነገረለት ታሪክ በወቅቱ መሪ ተዋንያን በነበርን ካድሬዎች ዘንድ የእሳት ዳር ጨዋታ ሆኖ ሰንብቷል።*

እንግዲህ ልብ እንበል። ህወሃት መራሹ የኢህአዴግ መንግሥት ወደ ሥልጣን የመጣው በ1983ዓ/ም ነበር። የደርግ ዘመነ መንግሥት ግፍና ፍጅት ገና ያልጠገገበት ወቅት። ሆኖም ህወሃት መራሹ መንግሥት አስር ዓመት እንኳን ሳይሞላው ለአስራ ሰባት ዓመት በኮረኔል መንግሥቱ አመራር መከራና ገፈት የተጋተው ህዝብ አዲሱን መንግሥት አልፈልግም ብሎ ከትከሻው ላይ አውርዶ ዘጭ አደረገው፤ በምርጫ ካርድ። እንደ 97ቱ ምርጫ የቀሰቀሰው፤ ያስተባበረው፤ አማርጫ መንግሥት እንሆንኻለን ያለው የለም። ግን ‘ምረጥ’ ተባለ። ምርጫውን አሳወቀ፤ ህወሃት ኢህአዴግን አንፈልግም ብሎ። ይህ ህዝብ እንደ ህዝብ በፖለቲካውና በሀገሩ አስተዳደረዊ ሂደት ላይ የበሰለና አርቆ ተመልካች ህዝብ መሆኑን አላስመሰከረምን? ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ትንታኔ በመስጠት የህወሃትን ፖሊስ እኩይነት የደሰኮረው የለም። በቴሌቪዥንና በሬዲዮ የሰበከው የለም። ግን ፖለቲካዊ ብይን የመስጠት ብቃት ያለው ጨዋ ህዝብ መሆኑን አሳየ። መሪ ግን አልነበረውም። ያለ መሪና ያለ ድርጅት ፖለቲካዊ ብይን የመስጠት ብቃቱን ያስመሰከረ ታላቅ ሕዘብ እንደ ሕዝብነቱ በሚሰነዘርበት አስተያየት “ሊከበር” አይገባውምን?

እንመለስ ወደ መልዕክተ ኤርምያስ፤

*በጨፌ ግምገማ ኢህአዴግ በመሸነፉ ላይ ጥያቄ አንስቶ የተከራከረ አልነበረም። ይልቁንስ ሽንፈቱን የሚያሳዩ ሰፋፊ መገለጫዎች ቀረቡ። የውጤቱ መቀልበስ ተከትሎ በመዲናይቱ ተከስቶ የነበረው አደጋ በሰፊው ተነገረ። **በተስፋ እጦትና የከተማ ችጋር የተመታው ነዋሪ አደራጅቶ የሚያንቀሳቅሰው ተቃዋሚ ቢኖር ኖሮ ዛሬ እንደዚህ ተቀምጦ ስለ አዲስ አበባ የምንነጋገርበት ሁኔታ እንደማይፈጠር ተገለፀ።** ምርጫውን ለመቀልበስ በተግባር የዋለው ፀረ ዲሞክራሲ ቢሆንም አብዮታዊ ዲሞክራሲን እንደታደገው አስተያየቶች ቀረቡ።*

*በተለይም የደህንነቱ ሹም ኢሳያስ ወልደ ጊዮርጊስ፤ 'የታደግናችሁ እኛ ነበርን' ብሎ በኩራት ሲደሰኩር መስማት አስገራሚ ነበር። በእያንዳንዱ ወረዳ በእሱ ፊታውራሪነት የተሰራውን ሸፍጥ በዝርዝር ማቅረቡ እንደ ዕውነቱ ከሆነ ከአንድ የደህንነት ሹም የሚጠበቅ አልነበረም፤ ምንም እንኳን ሀቁ እሱ የተናገረው ቢሆንም።*

መቼም ህወሃት መራሹ መንግሥት በሥልጣን እስከቆየ ድረስ 'የአብዮታዊ ዲሞክራሲ' ፍቺና ጣጣም እንደዘመኑ የተንዛዛና የተጣጠፈ ይሆናል። ከ92 ምርጫ ጀምሮ እንደታየው። የህወሃትን የደህንነት ሹም ካነሳን አይቀር በነካ እጃችን ስለ እሱ በተላለፈው መልዕክተ ኤርምያስ ላይ፤ ***ኢሳያስ የድንቁርና አክሊል ያጠለቀ የአቶ መለስ የቁርጥ ቀን ልጅ ነው፤*** ተብሎ ተፅፏል።

*መፅሀፈ* ኤርምያስ ስለ 92 ምርጫና ውጤት ወረዳ በወረዳ ከነመረጃዎቹ እየዘረገፈ አደባባይ አስጥቷል። ህወሃት ኢህአዴጋውያንም ከያሉበት ተጠራርተው የሽንፈታቸውን ግዝፈት፤ የመሸነፋቸውንም 'ምክንያት'ና በቀጣዩ ምርጫ (1997ዓ/ም) ምን ማድረግ እንደሚኖርባቸው በአብዮታዊ ዲሚክራሲ መነፅር ሲገመግሙ ከርመዋል። ሁሉም መልዕክተ ኤርምያስ ውስጥ ይገኛል። እነሆ ከሰፊው መረጃ አንዲት አብነት እንንቀስና ውጤት አልባውን የመጀመሪያውን ህዝባዊ ሠላማዊ አብዮት፤ ምርጫ 92ን እንሰናበት።

*ወደ ወረዳ 20 (ቄራና ጎፋ) ያመራው ካድሬ የተቃዋሚ አንድ እጩ አስወጥቶም፤ የግል ተወዳዳሪዎች በግፍ አስገብቶም ሳይሳካለት ቀረ።* ***የወረዳ 20 ህዝብ ኢህአዴግን ከወረዳም ከአዲስ አበባ ምክር ቤትም አባረረ።*** *የቄራና ጎፋ ህዝብ ኢህአዴግ ያቀረበለትን ዶክተር፤ ኢንጂነር፤ ጋዜጠኛና ከፍተኛ ነጋዴ ወደ ጎን ትቶ መቃብራቸው የተማሰ፤ በምርኩዝ የሚሄዱ፤ ማንበብና መፃፍ የማይችሉ የመኢአድ አባላትን መረጠ። ይህም ህዝቡ እንደ ወረዳ 24 (ኮልፌ ቀራንዮ እና ሌሎችም ወረዳዎች) ሁሉ ኢህአዴግ ላይ ያለውን የመረረ ጥላቻ የሚያሳይ ሆነ።* ***እንደ ዕውነቱ ከሆነ የስምየን ልጅም ሆነ አቶ መለስ ወረዳ 20 መጥተው ቢወዳደሩ ኖሮ ወይ ለክብራቸው ሲባል ኮሮጆ አስቀድሞ ይገለበጣል፤ አሊያም የሽንፈት ፅዋቸውን ይጎነጫሉ።***

<u>**ምርጫ 1997 ዓ/ም**</u>

*"የኢትዮጵያ ድንኳኖች ሲጨነቁ አየሁ።" (ትንቢተ ዕንባቆም፤ ምዕ. 3 ቁ.7)*

***<u>ለመነሻ፤</u>***

በ1997 ዓ/ም የኢትዮጵያ ህዝብ ሀገራዊ ራዕይ ያነገቡ መሪዎችና ድርጅት ነበረው። የማያጠያይቅ የማያከራክር ሀቅ፤ ቅንጅት! እስከዛሬም ተነግሮና ተፅፎ ያላባራውን የ19997 ዓ/ም ምርጫና ቅንጅት ታሪክ በዚህ ወፍ በረር ዳሰሳ አስፋፍተን እንድናቀርብ አቅማችንም መነሻችንም እንዳልሆነ ታዳሚ ይረዳናል። ነገር ግን በመፅሀፈ ኤርምያስ ይህ ወቅት በሰፊው ተነግሯል። በማያነቃንቁ መረጃዎች ታጅቦ በቅድመ ምርጫ የነበረውን የህወሃት ኢህአዴግ ዝግጅትና፤ በምርጫው ማግሥትና በኋላ የወረደውን ህወሃታዊ የበቀል ነበልባላዊ ሠይፍ እርቃን አውጥቷል። የበቀሉ እሳተ ገሞራ የፈነዳባት አዲስ አበባም ስትነድ ስትንቀለቀል እንደ ፊልም ቀርፆ ያሳያል። በምርጫው ውጤት ማግሥት ህወሃት የአንድ ወር አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ደንግጓል። በመቶ የሚቆጠሩ ሠላማዊ ሰልፈኞችን በጠራራ ፀሀይ በጥይት ቆልቷል። የቅንጅት መሪዎችን ሰብስቦ ቃሊቲ አውርዷል። በአስር ሺህዎች የሚቆጠሩ ዜጎች የቅንጅት ደጋፊ ተብለው በወህኒ ቤቶች ተዘግቶባቸዋል። በመላ ሀገሪቱ ፅልመት ወርዷል፤ የምፅዐት ዘመን ሆኗል…እልቂቱ፤ እስሩና የአፈና ዘመቻው በተወራራሽነቱ ከሌላ ዘመን የተቀዳ ይመስላል፤ በኢሕአፓ ላይ ከወረደው የደርግ ቀይ ሽብር ዘመን…

በዚህ ቅኝት የዳሰሳችን ቀስት እጅግ በተመጠኑት የዚህ ወቅት ሁነቶች ላይ ብቻ ይሆናልና እነሆ እንዲህ እንጀምራለን።

## የኢትዮጵያ ሕዝብ ለምን በቅንጅት ዙሪያ ቆመ?

ይህንን ጥያቄ መነሻ ያደረግነው መልሱን የሥርዐቱ ተዋናይ ካድሬ ከነበረው አንደበት እንሰማው ዘንድ በመውደዳችን ነው። ኤርምያስ እንዲህ ይላል፤

***ቅንጅትን የመሰረቱት ሰዎች ትክለሰውነት ከኢህአዴግ ካድሬዎች ገዝፎ መታየቱ፣ አንግበውት የነበረው ኢትዮጵያዊነት አጀንዳ፣ በምርጫ ክርክሩ ወቅት በአግባቡ ራሳቸውን መሸጣቸውና አማራጭ ፖሊሲ መያዛቸው የምርጫ 97 የፖለቲካ ምህዳር በሀገር ደረጃ ግልብጥብጡን አወጣው። መስከረም ሳይጠባ የምናሸንፍባቸው ምክንያቶች ተብለው በኢህአዴግ የቀረቡት ቁምነገሮች በዜሮ ተባዙ።***

ይህ ጠቅለል ያለ ምልከታ ነገር ግን ሲበተን አያሌ ዝርዝር መሰረተ ሀሳቦችን በመምዘዝ *በኢህአዴግና በቅንጅት መካከል ያለውን ገደል ልዩነት የሚያሳይ ሆኖ ይገኛል።* ህዝቡ በ92 ምርጫ ያጣቸውን የድርጅት፣ የመሪ፣ የኢትዮጵያዊነትንና አማራጭ ፖሊሲ አካታች… "የኔ" የሚለውን ቀጣዩን መንግሥት መሪዎች በአማራጭነት ማግኘቱን። ስለዚህ ከቅንጅት ጎን ቆሞ በአንድ ድምፅ ተቀናጅቶ ህወሃት/ኢህአዴግ ከሥልጣን ይውረድ ብሎ ፈረደ። ሆኖም ህጋዊው ፍርድ በፍርደ ገምድሎች ታረደ… መልዕክተ ዜናዊ በአብዮታዊ ዲሞክራሲ ጡሩንባ እየተነፋ በአግአዚ ጦር ፊታውራሪነት ክተት ሠራዊት ምታ ቅንጅት ሆነ…

## በምርጫው ዕለት ከተስተዋሉት ሁነቶች፣ ለቅምሻ

መልዕክተ ኤርምያስ እጅግ አስደማሚ የሆኑ በምርጫው እለት የታዩ የህዝብን ስሜት ገላጭ ታሪኮች በስፋት ለጦቢያ ልጆች ነግሯል። እነሆ አብነት፣

*ምርጫው በተጀመረ አንድ ሰዓት ሳይሞላው ካድሬው ጓደኛዬ "አለቀ፤ደቀቀ"፣ የሁሉ ደነቀ ደግሞ "እርሶ አደሩም አሰላለፉን ለውጧል" ብለው አለመረጋጋት ውስጥ ከተቱኝ። የተምታታ ሀሳብ ውስጥ ተጠምጄ ባለሁበት ሰዓት ከአንድ አቅራቢያችን ከሚገኝ ምርጫ ጣቢያ አንዲት ሙሽራ ቬሎዋን እንደለበሰች ለመምረጥ እንደተሰለፈች ተነገረኝ። የኩነት ኮሚቴውን ከሚመራው አባል ጋር ካሜራ ይዘን በፍጥነት ሄድን። እንደተባለው ሙሽሪት ቬሎዋን ቂቅ አድርጋ መስመር ይዛለች። ህዝቡ ቅድሚያ እያለ ቢያስገድዳትም አሻፈረኝ በማለት ቆማለች። ካሜራ የያዘው አባል ሙሽሪት አጠገብ ሄዶ መቅረፅ ሲጀምር የድል ምልክት በእጆቿ አሳየችው። ከጫፍ እስከ ጫፍ የተሰለፈው ህዝብ ያሰማው የድጋፍ ጩኸት ጆሮዬን አደነቆረው። ከመኻል መስመር አንድ ወጣት ጮክ ብሎ፣ "ሥነ ሥርዐት ልምን አታደርጉም? ኢህአዴግ ብጥብጥ ተነሳ ብሎ ምርጫውን እንዲያስተጓጉል ትፈልጋላችሁ? እባካችሁ እንደተነጋገርነው በሠላማዊ መንገድ ምርጫው እንዲፈፀም እናድርግ" አላቸው።*

***ከልጁ ንግግር በኋላ ጠጠር ቢወድቅ ይሰማ ነበር። ሁሉም ፊቱን ቅጭም አድርጎ አደብ ገዛ። በጠቆረው ፊት ውስጥ የሚንቀለቀለውን የለውጥ ስሜት ማንበብ ግን በቀላሉ ይቻል ነበር።***

ይህ የቀድሞው የኢህአዴግ ከፍተኛ ካድሬ፣ የመለስና የበረከት ቅርብ አካል (በየሳምቱ አብሯቸው ስብሰባ የሚቀመጥ) 'ኤክስ' ሚኒስትር ኤርምያስ ለገሰ በዓይኑ በብረቱ የተመለከተው፣ በራሱ ጆሮ የሰማው የምርጫ ትዕይንት - በደምሳሳው በመላ ሀገሪቱ ሰፍኖ ስለነበረው የለውጥና የአዲስ ዘመን ብሥራት ድባብ ፍንትው አድርጎ ያሳያል።

ሙሽርነት በህይወት ዘመን የአንድ ሰው አዲስ ህይወት ምዕራፍ መክፈቻ ወይም መጀመሪያ ነው። ሙሽሪት ይህንን የህይወት ምዕራፏን በዳስ ውስጥ አልያም በመዝናኛ ስፍራ ከዘመድ አዝማድ ከጓደኛ ጋር ሆና ከበሮ እየተደለቀላትና "የኛ ሙሽራ ኩሪባቸው..." እየተዘፈነላት ማሳለፍ አልፈለገችም። ወደ ምርጫ ጣቢያ ሄዳ መፃዒውን የሀገሯን የጉዞ አቅጣጫ ይቀይሳል ብላ ላመነችበት ምርጫ ቅድሚያ ሰጠች፤ ኢህአዴግን ሳይሆን ቅንጅትን አለች። ወይራው የአብዮታዊ ዲሞክራሲ ታጋይና አታጋይ ኤርምያስ ለገሰ ያየውንና የሰማውን ማመን አቃተው፤ አዙሮት አለመውደቁም ብርቱ ካድሬ መሆኑ!! ከዚህ ትዕይንት ጥላ ያልተላቀቀው ካድሬው ኤርምያስ፤ ብረሪ ያላት ደባል ነፍስ ይዞ፤ ደግሞ ሌላ ምርጫ ጣቢያ በረረ....

እና፤ ዳግም ያየውንና ዳግም የሰማውን ዘገበ፤ በመልዕክተ ኤርምያስም እንዲህ ከተበ...

*ጎፉ ገብርዔል ጋር ባለ ጣቢያ ለመውለድ ቀናት የምትጠብቅ ሴት ለመምረጥ በድጋፍ እንደመጣች ተነገረን። በወረዳው ለፓርላማ እየተወዳደረ ያለውን ገብረዋህድ (ገቢዎች ሃላፊ) ይዤ ወደ ቦታው ሄድኩኝ። ባጋጣሚ ሴትየዋ መርጣ ስትወጣ ደረስን። ካሜራውን የያዘው አባላችን ምርጫውን እንዴት እንዳገኘቻው ጠየቃት። እሷም መስመር ሰርቶ ወደሚጠብቀው ህዝብ እየተጠጋችና ሆዷን እየነካካች፤*

***'ነፃነቴን ሳታውጂ አልወለድም ብሎ አስቸግሮ ነበር። ልክ የድምፅ ካርዱን ሳስገባ ተፈራገጠ። ካልወጣሁ ብሎ አስቸግሯል። ዛሬ ማታ ከነነፃነቱ ይወለዳል።' በማለት ተናገረች። በጉጉት ሲያዳምጣት የነበረው ህዝብ ድንኳኑን በጭብጨባ አቀለጠው። ለካስ ህዝቡ አንድ አካል አንድ አምሳል ሆኗል። የነበረኝ እንጥፍጣፊ ተስፋ ሙሉ ለሙሉ ተሟጠጠ።***

እሰይ እንኳንም ተሟጠጠ።

ያ ህፃን!... 'እድሜ' ለመልዕክተ ዜናዊ፤ 'እድሜ' ለአብዮታዊ ዲሞክራሲ፤ 'እድሜ' ለህወሃት ኢህአዴግ ካድሬዎች፤ 'እድሜ' ለአጋዚ ነፍሰ በላ ጦር፤ 'እድሜ' ለአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ......ነፃነቱን ተቀዳጅቶ ይወለድ ዘንድ አልተቻለውም። እነሆ እስከ ዛሬም "እናቱ" ምጥ ላይ ናት። ነፃነቱን አውጇለት በነፃነት ትወልደው ዘንድ ዛሬም እንዳማጠች አለች። እንደውም መከረኛዋ "እናቱ" ማማጥ የጀመረችው ጥንት ነበር...ከ1950ዎቹ ጀምሮ። አቤ ጎበኛ እንደነገረን ከሆነ...

አቤ በድሮ ዘመን (አዎ! ድሮ እንበለውና) የኖረ ጋዜጠኛና ደራሲ ነበር። ሀገሩ ከፊውዳል ሥርዐትና ዘውዳዊ አስተዳደር ተላቃ፤ ከዓለም የሥልጣኔ በረከት ተቋድሳ፤ ህዝቦቿ በልፅገው፤ ነፃነታቸውና ሰብዓዊ መብታቸው ተከብሮ...ማየት የሚሻ፤ የዛ ዘመን ትውልድ ለውጥ አላሚ! እና ህልሙን ፃፈ፤ "አልወለድም" ብሎ...ያኔ፤ድሮ...

ጥቂት መስመሮችን እንቀንጭብ፤

መከረኛና ድሃዋ እናቱ "አልወለድም" ብሎ በምጥ የሚያስጨንቃትን ህፃን እንዲህ አለችው፤

*"ታዲያ ምን ይሻላል?"*

***"መብትሽን ለማግኘትና እኔንም ከነመብቴ ለመውለድ ሞክሪ"***

*"ስለፈጠረህ ብለህ ተወለድ!"*

*“ፈጣሪም የፈጠረኝ ለባርነትና ለችግር ከሆነ እሱንም አሻፈረኝ ብዬዋለሁ። እሱ የነፃነት ዓለም ፈጠረ። ግፈኞች ነፃውን ዓለም የባርነት ዓለም አደረጉት። ቂሎችና ደካሞችም ራሳቸውን የባርነት ማስፈሪያ ወደብ አደረጉት። መልካም! ባርነትን የሚሹ ባርያ ይሁኑ። የነፃነት ጠበቃ ስሆን “ባርያ የመሆን ነፃነት ይሰጠን” የሚሉትንም የወደዱትን ባርነት እንዲጠግቡት መተው አለብኝ። እኔን ወደ ባርነት ግባ ሲሉኝ ግን ታላቅ ጠብ መፈጠሩ ነው!” ስለዚህ ‘አሻፈረኝ፤ ለባርነት አልወለድም!’ ብሏል በይ! ሰውን ለመወንጀልና እምቢተኛ ነው ለማለት ዳኛ ሞልቷል። ዳኛ የማያገኙት ለነፃነት የሚሟገቱት ናቸው እንጂ ነፃነት ፈላጊዎችን ለመክሰስ የዓለም ፍርድ ቤቶች ሁሉ ክፍት ናቸው። ክሰሺኝ፡፤ ‘እምቢ አለ በይ!’*

እነሆ ይህ የአቤ ጎበኛ ‘አልወለድም’ ነው። ከ1997 ዓ/ም ምርጫ 40 ዓመት በፊት በምናብ የተፈጠረችው እርጉዝ እናት ታሪክ። በ1997 ዓ/ም ምርጫ አቤ ጎበኛ የፈጠራት ነፍሰ ጡር እናት በአፀደ ሥጋ ጎፋ ገብርኤል ተገኘች። የባርነት ጠበቆች ለሆኑት የኢህአዴግ ካድሬዎችም አለቻቸው ሆዷን እያሻሸች *…ነፃነቴን ሳታውጂ አልወለድም ብሎ አስቸግሮ ነበር…ዛሬ ማታ ከነነፃነቱ ይወለዳል…*

እነሆ ያን ማታ ህወሃት/ኢህአዴጎች የህፃኑን ነፃነት ቀርቅበው የጨለማ ዘመን ለመግባቱ በመልዕክተ ዜናዊ የአስቸካይ ጊዜ አዋጅ አወጁ…እንደ አሳሞቹ አምባገነንና ዘረኛ መንግሥት “ሁሉም እንስሳት እኩል ናቸው። ነገር ግን ጥቂት እንስሳት ከሌሎች ይበልጥ እኩል ናቸው”…ሲሉ የአዋጅ ነጋሪት ጎሰሙ ። የዚህ አባባል ፍቺ የእኛን ትንተና አይሻም።

ለመሆኑ ይህቺ መከረኛ እናታችን፤ ይህቺ ዞሮ መግቢያ ሀገራችን ኢትዮጵያ እስከመቼ ስታምጥ ትኖራለች?!

****************

ለጊዜው የቅኝት ቀስታችንን እናዙርና…እስቲ በዚህ የ97 ብይነ ምርጫ ቀን ካድሬው ኤርምያስ ምን ተሰማው? ብለን እንጠይቅ።

ግንቦት 7፤ በምርጫው እለት፤ የኤርምያስ ወላጅ እናት 80ኛ ሙት ቀን መታሰቢያ/ተዝካር ነበር። የአብዮታዊ ዲሞክራሲ ባልዲ በአፍጢሙ እየተደፋ በመሆኑ ይጨብጥ ይለቀው የጠፋው ወይራው አብዮታዊ ዲሞክራት የቀረችውን እንጥፍጣፊ በልቡ ቋጥሮ የመልዕክተ ዜናዊ ድቤ ከሩቅ ሲጎሰም እየተሰማው በእናቱ 80ኛ ተዝካር የቆመውን ሀውልታቸውን ለማየት ወደ ‘ሙታን መንደር’ ሄደ። ይህ ቀን በመልዕክተ ኤርምያስ እንዲህ ተፅፏል፤

*ጠዋት ሁለት ሰዓት የእናቴን መቃብር ለማየት ቀጠሮ ይዣለሁና ወደ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ሄድኩኝ። ከቄራ፤ ጦርሃይሎችና የወይራ ሰፈር መንገዶች በሰው ተሞልተዋል። ባለፍኩባቸው ቦታዎች የሚገኙ ምርጫ ጣቢያዎች በሰልፍ ተጨናንቀዋል። ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ስደርስ ከወትሮው ጭር ብሏል። የሙታን መንደር ፀጥ ሲል ያስፈራል። እነሱም መቃብሩን ፈንቅለው የአዲስ አበባን የለውጥ ንፋስ እየተቋደሷት እንደሆን ተሰማኝ። ምናልባት ከሌላው በተለየ “ልጄ ይመጣል” ብላ የተጫነባትን ድንጋይ ያላነሳችው እናቴ ትሆናለች። ርግጥም ወደ መቃብሯ ስደርስ ያልደረቀ ነጭና ጥቁር ቀለም የተቀባው ሀውልት የእሷ ነበር። ዛሬ! ሰማንያ ቀኗ ነው። በኦርቶዶክስ ዕምነት ሥርዐት መሰረት ቁርባኗ (ተዝካር) የሚወጣበት ቀን። ከሰዓታት በፊት ከልጆቿ የተበረከተላት ጉንጉን አበባ ሽታው ከሩቅ ይጣራል። እኔም ደረብኩላት። ስቅስቅ ብዬ አለቀስኩ።*

*የውስጤ ጩኸት ጆሮዬን አደነዘዘው። የ”ጴጥሮስ ያቺን ሰዓት” ታሪካዊ ተውኔት መነባንብ ወደ ራሴ ገለበጥኩት። እናም በሙታን መኻል ቁጭ ብዬ እንዲህ በማለት ጮህኩ፤*

*አዎን ብቻዬን ነኝ ፈራሁ*
*እሸሸግበት ጥግ አጣሁ*
*እምፀናበት ልብ አጣሁ።*

******************

ይህ ሰው፤ ሰው የሚሸት፤ ልብን በሀዘን የሚያኮማትር የሰቀቀን ጩኸት ነው። በሙታን መንደር የሚገኙ ሙታን ሁሉ መቃብር እየፈነቀሉ ከሕዝብ ጎን የቆሙ ሲመስለው እናቱ ብቻ የተጫነባቸው ድንጋይ እንደተጫነባቸው እንዲቀር መፈለጋቸው ተሰማው። ለምን? ብለን አንጠይቅም፤ እንደ ጠዋት ጮራ የተፈነጠቀ እውነት ያውቃሉና! ይህንን ለቅሶ ያለቀሰችው የአብዮታዊ ዲሞክራሲ ፈታውራሪዋ የኤርምያስ ደባል ነፍስ፤ አይደለችም። በሙታን መንደር የተገኘችውና የሲያልን በር ለመበርገድ ህቅ! ብላ ያነባቸው ደራሲ ነፍሱ ነበረች፤ በደባል ነፍስ ተማርካ በእግረ ሙቅ መቀመቅ የወረደችው ቀዳሚት ነፍሱ። እናም ስለ እናቱ አለቀሰች። ስለ ሌሎች እናቶችም ሁሉ አለቀሰች። ስለ ሙታንም ሁሉ አለቀሰች። በነፃነት መወለድ ስላልቻሉትም ሁሉ አለቀሰች። በነፃነትም መኖር ስላልቻሉት ሁሉ አለቀሰች። እሷን ስለሚመስሉትም ሁሉ አለቀሰች። ስለራሷም አለቀሰች። …

በቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ሙታን መንደር ተገኝታ ያነባችው ደራሲ ነፍስ ከዚህች ቀን በኋላ እንኳን ነፃነቷን ለመቀዳጀት አራት ዓመት እሪ! ስትል ኖራለች፤ በድምሩም አስራ ሁለት ዓመት!!

******************

እነሆ ወደ ቀደመ ጉዳያችን ተመልሰናል።

<u>ምርጫ 2000 ዓ/ም</u>

እነሆ በአዲስ ኪዳን ቆጠራ ክርስቶስ ከተወለደ ሁለት ሺህ ዓመት ሆነው፤ ያለፈው አንድ ሺህ ዓመት ተጠናቆ ኢትዮጵያም የሁለት ሺውን ዘመን ብሥራት ችቦ አብርታ፤ አበባ ዘንጥላ ተቀበለች። አበባየሁ ወይ አለች። አዲሱ ሚሌንየም ገና እንደገባ አበባዋን አደረቀው። ችቦዋን የጋን ውስጥ መብራት አደረገው፤ ህወሃት መራሹ ኢህአዴግ። የጠቢያን የአዲስ ዘመን ብሥራት ችቦ አጥፍቶ እሱ በ'ንቧ' ምትክ 'ችቦ' ይዞ ቀረበ፤ ኢህአዴጋዊ አርማዬ ከእንግዲህ 'ችቦ' ነው ብሎ። ለምን? ቢሉ - *በምርጫ 97 ህዝቡ የኢህአዴግን መለያ "ንብ" ሲመለከት 'ዝንቧ' መጣች እያለ ስለሸሻቸው፤* ይላልና መፅሀፈ ኤርምያስ።

የኢትዮጵያ መዲና የአዲስ አበባ ነዋሪ ሕዝብ (ከ92 በኋላ) ለሁለተኛ ጊዜ ያለ መሪና ያለድርጅት ብቻውን ታግሎ ህወሃት/ኢህአዴግን አሸንፎ ተሸነፈ፤ በምርጫ 2000 ዓ/ም።

መልዕክተ ኤርምያስ እንዲህ ተላልፏል፤

*ለአባሎቻችን የኢህአዴግ ምልክት ከእንግዲህ በኋላ "ችቦ" መሆኑን በመንገር የተለያዩ ፈጠራዎችን ተጠቅማችሁ አስተዋውቁ ብለን ስምሪት ሰጠን። እናም ለፈጠራ የተፈጠሩት አባሎቻችን የምርጫው እለት ቅስቀሳቸው "አይስክሬሚን ልሳችሁ ውጡ" የሚል ሆነ፤ (ችቦው የአይስክሬም ቅርፅ ስላለው)። በቊርቆስ የሚቀሰቅስ አንድ እሳት የላሰ ካድሬ አንድ እናት በአጠገቡ ሲያልፉ ጠጋ ብሎ፤*

*"ማዘር እንዳይረሱ አይስክሬሚን ነው ልሰው የሚወጡት" ይላቸዋል። ማዘርም ዋዛ አይደሉምና፤*

*“አይ ልጄ! በባዶ ሆድ አይስክሬም? ቀኑን ሙሉ ከሚያስመልሰኝ እንደለመድኩት ጦሜን ብውል ይሻለኛል” አሉት። ጦም ውላ ያደረች የምርጫ ወረቀት ሳጥኑ ውስጥ አኑረው ሄዱ። ይህ ተግባር የአስር ሺህ እናቶች ሆኖ ዋለ።*

ጉድ ሳይሰማ መስከረም አይጠባም ነበር ብሂሉ፤ ግና መስከረም ጠብቶም ጉድ ተስተዋለ። እነሆስ ማን ነው በሀገሩ ፖለቲካ ሳልሳዊ ጨዋ ፍርድ በህወሃት መራሹ ኢህአዴግ ላይ የፈረደው?! “ተኝቷል” የሚባለው ግና እንቅልፍ በዓይኑ ሳይዞር የኖረው አስተዋዩ የኢትዮጵያ ሕዝብ።

መልዕክተ ኤርምያስን እንቀጥላለን፤ እንዲህ ተፅፏልና፤

*እኩለ ሌሊት ሲቃረብ በረከት (የስምዖን ልጅ) ተፈራ ዋልዋና ሚስቱ ጥለውን ሄዱ። የመርካቶና የካ ካድሬዎች አለቃ የሆኑት ሺሰማና ፈለቀ ተቀላቀሉን። እነ ሺሰማ በዛ እኩለ ሌሊት ሲመጡ የምሥራች ይዘው አልነበረም። የአዲስ አበባ ህዝብ ለሶስተኛ ጊዜ ቀለደብን አሉን። ምርጫ 92፤ ምርጫ 97፤ ምርጫ 2000። የቆጠራ ሂደቱን በአካል ተገኝቶ ለማየት ወጣሁ። የምርጫ ታዛቢዎች ወረቀቱ ላይ የሰፈረውን ምልክት በማየት በሶስት ጎራ ይመዘግባሉ - ኢህአዴግ፤ ተቃዋሚና ድምፅ አልባ - በማለት። በመላው አዲስ አበባ (የምርጫ) ጣቢያዎች የሚመራው “ድምፅ አልባ” የሚለው ነበር። በድምፅ አልባ ወረቀቶች ላይ የሰፈረው ፅሁፍ - “ኢህአዴግ ሌባ!”፤ “ኢህአዴግ ዘረኛ!”፤ “የደም ሥልጣን”፤ “ሆዳም!” ይላል።*

ታዲያስ! ራሳቸው ህወሃት ወኢህአዴጋውያን እንዳመኑት ማነው አሸናፊው? ማን ነው “ኢህአዴግ ሌባ!’፤ “ኢህአዴግ ዘረኛ!” ብሎ የፃፈና ደምፁን ያሰማ? ከሕዝብ አብራክ የወጣው፤ በዘመነ ህወሃት ኢህአዴግ ያደገው ወጣት ትውልድ! ይህ ወጣት ትውልድ በአጋዚ ጦር በጥይት አልተቆላምን? ይህ ወጣት ትውልድ በገፍ በግፍ እስር ቤቶች ተግዞ አልማቀቀምን? ዛሬስ በየቃልቲውና፤ ቂሊንጦ የሚማቅቀው የዚህ ወጣት ትውልድ አካል አይደለምን? አደራጅና መሪ ሲያገኝ (ወይም ያገኘ ሲመስለው) ማነው ንቅል ብሎ ወጥቶ አደባባዩን በተቃውሞ ሠልፍ የሚያናውጠው? ማን ነው ‘በሽብርተኛ ስም’ ከሀገሩ እንዲሰደድ እየተደረገ ያለው? ማን ነው የሕዝብን ብሶት ስላስተጋባ/ስለፃፈ ዘብጥያ እየወረደ ያለው?... እናም ከዚህ ዕውነታ ተነስተን - የዘመኑን ወጣት  ትውልድ በጅምላ የሚወቅሱትን - እንጠይቅማለን እንሞግትማለን፤ ዕውን ይህ ወጣት ትውልድ ግፍና በደልን አሜን ብሎ በትዕግሥት ተቀብሎ እየኖረ ነውን? . . . በማለት።

እነሆ መልዕክተ ኤርምያስን እንቀጥላለን፤

*ይህ ጥሬ ሀቅ /የ2000 ዓ/ም ምርጫ ውጤት/ የተደበቁ ዕውነቶችን ፍንትው አድርጎ ያወጣ ነበር። በአንድ በኩል ነዋሪው በተለይም ወጣቱና የተማረው ክፍል በድጋሚ ኢህአዴግን እንደማይፈልግ አረጋግጧል። በተጨማሪም ሕዝቡ ከኢህአዴግ በላይ ለምርጫ የቀረቡትን ተቃዋሚዎች እንደሚጠላ አሳይቷል። በሌላ በኩል እኛ ኢህአዴጎች ከአስር ሚሊዮን ብር በላይ አውጥተን ከዘረጋነው ኔትዎርክ በላይ ውስጥ ለውስጥ የተደራጀ ህቡእ መንፈስ መኖሩን አመላክቷል። ይህ ውስጥ ለውስጥ የተደራጀ መንፈሳዊ ኔትዎርክ በከተማዋ ገጠር ቀበሌዎች ሳይቀር የተዘረጋ ሲሆን በከተማው አርሶ አደር አካባቢ “ኢህአዴግ ሌባ” “ሆዳም!” ተብሎ የተፃፈበት ወረቀት ማግኘት ምን ያህል ወደ ህብረተሰቡ ዘልቆ የገባ መሆኑን የሚያሳይ ነበር። እንደ እውነቱ ከሆነ በምርጫ 97 የነበረው ቅንጅት ሳይሆን መንፈሱ፤ በኢትዮጵያ ሕዝብ ውስጥ ያለው የለውጥ ፍላጎት ነው። ይሄ መንፈስ ዛሬም በኢትዮጵያ ምድር አለ።*

አዎን እናምናለን። ዕውነት ነው በኢትዮጵያ ሕዝብ ልብ ውስጥ የሚነድ፤ የሚንቀለቀል የለውጥ ፍላጎትና ረመጥ እንደ 92ቱ እንደ 97ቱ እንደ 2000 ዓ/ምህረቱ ዘንድሮም አለ። ያለ ፍጅትና ያለ እርስ በርስ ትልልቅ /ሲቪል ዋር/ (በተወሰነ መስዋዕትነት ግን ሊሆን ይችላል) አምባገነኑን፤ ሌባውንና ሆዳሙን ህወሃት መራሹን

የኢህአዴግ መንግሥት ለመለወጥ የኢትዮጵያ ሕዝብ “ሠላማዊ አብዮት/ለውጥ” ማካሄድ ይፈልጋል።

“ሠላማዊ አብዮት” ወይም “ሠላማዊ የለውጥ ትግል” ምንድን ነው? ብለን በመጠየቅ ከመነሻችን የሚያስወጣን ትንታኔ ውስጥ መግባት አንፈልግም። ቅርንጫፉ ብዙ ከመሆኑ አንፃር እንደ ሂሳብ ቀመር አንድ ወጥ የሆነ መነሻና መታያ የለውምና። ደግሞም በቀድሞው ዘመን (ለምሳሌ በህንድና በዘረኛዋ አሜሪካ) እንደየሀገራቱ ሶሺዮ ፖለቲካ ጭብጥና ዕውነታ ያገለገለው ሠላማዊ አብዮት (ሠላማዊ ትግል) በዚህ ዘመን ለሌሎች ሀገራት እንደፎርሙላ ሆኖ ሊያገለግል አይችልም። ለአብነት የቅርብ ዘመኖቹን “የቀለም አብዮቶችን” አነሳስና ታሪክ መመልከት ይቻላል። ነገር ግን ቀጣዩን በአፅንዖት መናገር እንወዳለን።

አምባገነኖችና ጨቋኞች በሚመሩት መንግሥት ውስጥ ሕዝብ ህሊናዊ መብቶቹን ተገፍፎ፣ በሰላዮችና ፖሊሶች ተከብቦ፣ ወኪሎችህን “ምረጥ” ሲባል - በምርጫ ካርዱ ላይ መብቱን የገፈፉትን፣ በሰላዮች የከበቡትንና፣ በሀይል የሚገዙትን አምባገነንና ጨቋኞችን አለመምረጡን ካሳወቀ፣ ይህ የሠላማዊ አብዮት ወይም ሠላመዊ ትግል አካል መሆኑን!! በመንግሥትነት አንፈልጋችሁምና በሠላም ሥልጣናችሁን ልቀቁ! በማለት ፍላጎቱን መግለፁ። *የኢትዮጵያ ሕዝብ እንደ ሕዝብ በመላዋ ሀገሪቱ በ97 ምርጫ፣ እንዲሁም የመዲናይቱ የአዲስ አበባ ሕዝብ ያለመሪና ያለ ድርጅት በምርጫ 92 እና 2000 ዓ/ምህረቶች በሠላማዊ አብዮት (በሠላማዊ የለውጥ ትግል) ህወሃት መራሹን የኢህአዴግ መንግሥት አሸንፏል። ምረጡ ካላችሁን በሠላም ሥልጣናችሁን እንድትለቁ እንፈልጋለን ሲል ምርጫውን ገልጧል፣ ከአንድም ሁለት ሶስቴ።* ይህ የሠላመዊ አብዮት/ለውጥ ትግል ለምን ውጤታማ አልሆነም? ለሚለው ደግሞ አጭሩና እውነታው መልስ እንዲህ ነው…

*ሕዝብ እንደ ሕዝብነቱ ድርጅት ፈጣሪ አይደለም።* ድርጅትን ፈጣሪዎች ለህዝብ መብትና ለመልካም ሀገራዊ አስተዳደር አማራጭ ሀይል እንሆናለን የሚሉት “ምሁራን” ወይም “የተማሩ ሰዎች” የሚባሉት ናቸው። ለሕዝብ ቆመናል የሚሉ ድርጅቶች (ወይም ነጠላ ድርጅትም ሊሆን ይችላል) ሕዝብ አመኔታ በሚጥልባቸው መሪዎች እየተመሩ ሕዝቡን ከጎናቸው በማቆም ሕዝባዊው ማዕበል ማረፊያ ወደብ ወይም ውጤት እንዲኖረው ማድረግ ይችላሉ።

ህዝባዊ ነውጥ በመኪና ሞተር ይመሰላል። ሕዝብ የለውጥ ሞተር ነው። ሞተር ግን መሪ ከሌለው በራሱ ወደ ተፈለገበት ቦታ አያደርስም። የለውጥ ሞተር የሆነው ሕዝብ መሪና ድርጅት ያስፈልጉታል። የለውጥ ሞተር ያንቀሳቀሰ ሕዝብ መሪና ድርጅት ከተገጠሙለት/ካገኘ በትግሉና በመስዋዕትነቱ መሪዎቹንና ድርጅቱን ይዞና ተከላክሎ ወደ ወደቡ ያመራል እንጂ ወደቡ ላይ የሚያወጡት መሪዎቹና ድርጅቱ ናቸው። ይህንን ማድረግ የቻለ ድርጅትና መሪ ውጤት ያስመዘግባል፣ የሕዝብ ትግል ውጤት።

በኢትዮጵያ ከ1966 ዓ/ም ሕዝባዊ ሠላማዊ አብዮት ጀምሮ ይህ ሊሆን አልቻለም። የኢትዮጵያ ሕዝብ የለውጥ ሞተር ሆኖ ለመነሳት ወደኋላ አላለም፣ አይልም። ያጣው መሪና ድርጅት ነው። መሪና ድርጅት ያጣው የኢትዮጵያ ሕዝብ በተደጋጋሚ አሸንፎ በመሸነፉ፣ ለህወሃት መራሹ የኢህአዴግ መንግሥት ዕድሜ መርዘም ተጠያቂ አድርጎ መውቀስ ከቶም አግባብ አይደለም። ይህ ታላቅ ሕዝብ ግን የራሱ በሆነ ብቸኛ ነጠላ ዜማ እንዲህ እያለ ሳያንጎራጉር ይቀራል? *ከአንድም ሁለት ሶስቴ ምርጫ ተብለናል፣ ከአንድም ሁለት ሶስቴ “ንብ” “ችቦ” ጥለናል!*

## ክፍል አምስት

## የስምየን ልጅ ተደቆሰ

-------------//----------------

*"ክፉውን መልካም፣ መልካሙን ክፉ ለሚሉ፣ ጨለማውን ብርሃን፣ ብርሃኑንም ጨለማ ለሚያደርጉ፣ ጣፋጩን መራራ፣ መራራውንም ጣፋጭ ለሚያደርጉ ወዮላቸው! ጨካኞች ለሆኑ፣ በደለኛውን ስለ ጉቦ ፃድቅ ለሚያደርጉ፣ የፃድቁን ፅድቅ ለሚያስወግዱበት ወዮላቸው!" (ትንቢተ ኢሳይያስ፣ ምዕ. 5 ቁ. 20 — 23)*

-------------//-----------------

'ከመምህሩ ደቀመዝሙሩ" ይላል ብሂሉ። እንግዲህ በዚህ ክፍል ውስጥ መምህሩ የስምየን ልጅ፤ ደቀመዝሙሩ ደግሞ ኤርምያስ መሆናቸው ነው። ያኔ በ1983 ዓ/ም በወርሃ ግንቦት ህወሃት/ኢህአዴግ (ከኤርትራና ትግራይ ተነስቶ) ከነጎሬሬው አዲስ አበባ ሲገባ የስምየን ልጅ የአዲሱን መንግሥት ጥንስስ ይዘው አራት ኪሎ ከገቡት አንዱ ነበር። ያኔ ኤርምያስ ከት/ቤት ወደ ቤት የሚመላለስ የአዱ ገነት (የአዲስ አበባ) ታዳጊ ጉብል ነበር። በቃ!

ታዳጊው ኤርምያስ አድጎ የስምየን ልጅ የማደጎ ልጅ ሆነ።

እነሆ ደግሞ ዘመን አለፈና መምህሩ የስምየን ልጅ በደቀመዝሙሩ ኤርምያስ 'አራት ክንድ' ተደቆሰ። ሁለቱን ክንድ የተዋሰው ከራሱ ከመምህሩ ነው፤ ሁለቱ ደግሞ የራሱ የደቀመዝሙሩ። 'የስምየን ልጅ' እያለ የሚጠራው ራሱ ደቀመዝሙሩ ኤርምያስ እንጂ እኛ አይደለንም። የስምየን ልጅ ስሙ በረከት ነው። ኤርምያስ ለምን 'የስምየን ልጅ' ብሎ አሳዳጊውን ይጠራዋል? እንግዲህ እንደምንጠረጥረው ብቻ ሳይሆን እንደምናምንበትም 'በረከት' ለግብሩ የሚመጥነው ስም ባለመሆኑ (በቀዳሚ ገፆች ያቀረብነውን እግዜሩን ያስታውሷል) ፣ ሀገርና ሕዝብን በረከት አሳጥቷልና፤ ብዙ ምሥጢር ተካፋዩ የነበረው ደቀመዝሙሩ፤ የስምየን ልጅ ብሎ ተለዋጭ ስም ገጥሞለታል። እኛም ወደንለታል።

"ይሉኝን በሰማሽ ገበያ ባልወጣሽ" ይላል ተረቱ፤ የመሰረቱ። ሆኖም የስምየን ልጅ የኤርምያስ ደባል ነፍስ ከአብዮታዊ ዲሞክራሲ ማተቧ ጋር እንጦርጦስ መውረዷን ሳይረዳ "የሁለት ምርጫዎች ወግ" ብሎ ወግ ጠረቀ። ጠርቆም ገበያ ወጣ። እነሆም ከስምየን ልጅ ማደጎ ልጅነት ተላቃ ራሷን የቻለችው የኤርምያስ ደራሲ ነፍስ ደግሞ 'ድንጋይ ዳቦ ብለህ መርካቶ ከወጣህ፤ መደብ እንዲሆንህ ብረት ምጣድ ልስጥህ!" ብላ አንቀረቀበችው ጥዳ፤ በመለስ ትሩፋቶች። እነሆ ከመልዕክተ ኤርምያስ እንጠቅሳለን፤

*የኢህአዴግ ፕሮፓጋንዳ የሚመራባቸው መርሆዎች በአብዛኛው የሚመነጩት ከጀርመናዊው ፕሮፓጋንዲስት ጆሴፍ ጎብልስ ነው። ጎብልስ በዘመነ ሂትለር ተለያዩ መርሆዎችን በመቀረፅ በተግባር ላይ አውሏል። ከነዚህም ውስጥ ፕሮፓጋንዳ በታቀደ መልኩ በአንድ ተቋም፣ በተመረጠ መሪ ቃል መመራት እንዳለበትና ተደጋጋሚ በሆነ መንገድ (አሰልቺም ቢሆን) መገለፅ እንዳለበት ያስገነዝባል። የጎብልስ ፕሮፓጋንዳ ማጠንጠኛ (the big lie theory) በመባል ይታወቃል። የሀገራችን ሰው "ውሸት ሲደጋገም ዕውነት ይሆናል" እንደሚለው።*

*ኢትዮጵያዊው ጎብልስ ሶስት ገፆችን አጣምሮ የያዘ ነው። ዕውነት፣ ዕውነትና ውሸት፣ ውሸት። ከእነዚህ ውስጥ ዋና ዋናዎቹ " የኢህአዴግ ሥልጣን የዛፍ ላይ እንቅልፍ ነው"፣ "ባለ ሁለት አሃዝ ዕድገት"፣ "የትራንስፎርሜሽኑ መሀንዲስ"...(ይገኙበታል)*

“አጃኢብ!” ይላል ሀረሪው፤ ገራሚ ነገር ሲገጥመው። እነሆ ጎብልሳዊው የህወሃት/ኢህአዴግ ፖሮፓጋንዳ፤ በቀድሞው የኮሙዩኒኬሽን ምኒስትር ደኤታ። አዎ፤ ዕውነት ነው “ውሸት ሲደጋገም ይሆናል ዕውነት” ያሉት አበው። ለአብነት “የሁለት አሃዝ ዕድገት” የሚለው ያላሰለሰው ህወሃታዊ ፕሮፓጋንዳ፤ እንኳን እኛን ምድረ ፈረንጅን አደንዝዟልና። ለካስ እኒያ አበው ሊቅ ነበሩ፤ የቀለም ዘር ሳይዘሩ፤ ዘምን ተሻጋሪ ሀቅ የዘሩ። ምናለ በዛሬ ዘመን ጥቂቱ እንኳ በኖሩ?!

እንመለስ ወደቀደመ ጉዳያችን፤

*ኢህአዴግ እራሱ በፈጠረው ባህር የሚቀዝፍ፤ መነሻው መድረሻ የሆነበት ድርጅት ነው። ይህ ባህር የራሱ የሚባሉ የቀዘፋ ሕግጋቶች አሉት። ስለነዚህ ሕግጋት አጠናቆ ለመፃፍ ቢያንስ ሶስት ጊዜ መወለድ ሊያስፈልግ ይችላል።*

*ሕግጋት አንድ፤ ዕውነት የተደጋገመ ኩሸት ነው። ከኢህአዴግ ጋር ያቆራረጠኝ፤ ከራሴም ጋር ቅራኔ ውስጥ የዘፈቀኝ ሕግ ይህ ነበር። ማስረጃ ካስፈለገ ከመልዕክተ ዜናዊ አልያም ከትንቢተ ስምዖን መጠቃቀስ እችላለሁ። ለዛሬው ፅሁፌ (የመለስ ትሩፋቶች፤ ባለቤት አልባ ከተማ) መነሻ የሆነኝ ከነዚህ ድርሳናት አንዱ የሆነው ገድለ ኢህአዴግ ነው። ይህ ገድል የሁለት ምርጫዎች ወግ የሚል ስያሜ ተሰጥቶታል።*

*(ለምሳሌ) በትንቢተ ስምዖን መልእክት ላይ “የአዲስ አበባ ሕዝብ አይጠላንም፤ ጠልቶንም አያውቅም” ሲል መጀመሪያ አካባቢ ከተዛባ ኢንፎርሜሽን ሊሆን ይችል እንደሆነ ተጠራጠርኩ። የስምዖን ልጅን በቅርብ ከሚያውቁት አንዱ ስለሆንኩና ምን አይነት መረጃዎች እንደሚደርሱት ስለማውቅ ጭምር። ትንሽም ሳልቆይ ሌላ ክፍል ላይ፤ “እኛ ኢህአዴጎች እንደ ሕዝብ የምንፈራው የለንም፤ ጌታችንም ሕዝባችን ነው። ባለፉት ዓመታት በጎ ነገር በመስራት ሉዐላዊ የሥልጣን ባለቤት የሆነውን የሀገሪቱን ጌታ ለማስደሰት ጥረት አድርገናል።” የሚል ተፅፎ ሳነብ ደነገጥኩ። እጄን በጭንቅላቴ ላይ አገኘሁት።*

*ስለየትኛው ኢህአዴግና ሕዝብ እያወራ እንደሆን ግራ ገባኝ። እነዚህ ሕዝብ የተባሉት ውስጥ በቅርብ የማውቃቸው የአዲስ አበባ ነዋሪዎች ፊት ለፊቴ ተደቀኑ። የአዲስ አበባን መከራና ብሶት ኖሬበታለሁ። ኢህአዴግ የመዲናይቱን ነዋሪዎች በመናቅና በማዋረድ የሰራውን ወንጀሎች አይቻለሁ። በከተማዋ ነዋሪዎች ላይ የተፈፀሙ ፀረ-ዲሞክራሲ ተግባሮች ተነግረው አያልቁም።*

እነሆ እንግዲህ መፅሀፈ ኤርምያስ የስምዖን ልጅ የኩሸት ጥርቅም የጠረዘበትን ‘የሁለት ምርጫዎች ወግ’ ከራሱ አንደበት እየቀዳ በመረጃዎች በታጀበ ሙቀጫ ውስጥ ሲደቁሰው፤ ሲያሸውና ሲበትነው እናገኛለን፤ ድንቅ ነው። የስምዖን ልጅ ሲዋሽ ለነገ አይልም። ይሉኝታና ትዝብት ብሎ ነገር በሰውየው ውስጥ አልተፈጠሩም። የስምዖን ልጅ የጠረዘው “የሁለት ምርጫዎች ወግ” ‘መፅሀፍ’ በመፅሀፈ ኤርምያስ ከገፅ አንድ (እንደ መነሻ ከቀረበው) ጀምሮ እስከ መፅሀፉ ፍፃሜ ድረስ በየክፍሎቹ፤ በየምእራፋቱና በየንዑስ ርዕሶች ውስጥ ሁሉ እየተነቀሰ በአራት መቶ ገፆች ተናኝቶ ሲወቃና ሲበራይ ማስተዋል፤ ኢትዮጵያን ስለሚመራት የህወሃት/ኢህአዴግ መንግሥት ምንነት ከዚህ ቀደም ከነበረን ግንዛቤ በላይ ገዝፎ እንድንገነዘብ ሲያስገድደን በዛው ደቂቃና ሰዓትም መላ ሰውነታችንን አንዳች ፅላላዊ ስሜት እንዲወረን ያደርገናል። ኢትዮጵያ እየሰጠመችበት የምትገኝበትን ዕውነታ!

የስምዖን ልጅ የናዚው ጎብልስ ደቀመዝሙር ብቻ አይደለም። የስምዖን ልጅ ጣዖት አምላኪም ነው። እነሆ መረጃችንን ከመልዕክተ ኤርምያስ እናስተላልፋለን፤ እንዲህ ተፅፏልና፤

*በረከት አቶ መለስን በተመለከተ ከልቡ የሚያምንበትን እንደተናገረ ያረጋገጥኩት በቅርብ ከእሱ ጋር መስራት ስጀምር ነበር። አቶ መለስ ለበረከት የልቡ ላይ አለት፣ የዘላለም ርስቱ፣ አልፋና ኦሜጋው ነው። እጅግ በጣም እርግጠኛ ሆኜ መናገር የምችለው ነገር ቢኖር አቶ መለስ ለበረከት የሰው ዘር አይደለም። ለጠቅላይ ሚኒስትር ሃይለማርያም "ዘላለማዊ ክብር ለታላቁ መሪያችን" የሚል "መልዕክተ ዜናዊ ወደ አቢሲኒያ" ሰዎች ፅፎ እየሰጠው በተከበረው ፓርላማ ዘላለማዊነቱን የሚያፀናለት እንጂ!!*

እነሆ ጣዖትን በማምለክ በአደባባይ ከጣዖት ማምለኪያው ማማ ላይ ቆመው መጀመሪያ መናፍቅነትን ያወጁትን አቶ ሃይለማርያም ደሳለኝን ያስታውሷል፣ መስከረም 5 ቀን፣ 2005 ዓ/ም የተናገሩትን፣ ***ዘላለማዊ ክብርና ሞገስ ለታላቁ መሪያችን ይሁን!***

ሃይማኖተኛ የተባሉትና፣ የፕሮቴስታንት ዕምነት ዘርፍ የሆነው "ኢየሱስ ብቻ አፖስተሊክ ቸርች" ተካታይ ጠ/ሚኒስትር ሃይለማርያም እነሆ የጣዖት አምላኪው የስምዖን ልጅ ተከታይም ናቸውና ዘወትር ለዜናዊ ልጅ "በመለስ ራዕይ" "ዘላለማዊ ክብርና ሞገስን" እንደለመኑ አሉ። ፀሎተ ዜናዊን ህወሃት/ኢህአዴጋውያን ሁሉ ማዕልት ከምሽት በፓርላማቸው እየተገኙ የሚያደርሱት ሆኗል። ግና ወዮላቸው!

ወዮ ለሃይለማርያም። ወዮ ለስምዖን ልጅ። ወዮ ለጣዖት አምላኪያን ህወሃት/ኢህአዴጎች! በታላቁ መፅሀፍ እንዲህ ተፅፏልና፣

*እግዚአብሄርን ካለማወቃቸው ጋራ ስህተታቸው አልበቃቸውምና ልጆቻቸውን ለጣዖት ይሰዋሉና። ሥራዎቻቸው ሁሉ ደም ከማፍሰስ ጋራ፣ ነፍስ ከመግደል ጋራ፣ ከመስረቅ ጋራ፣ ከሀሰት ጋራ፣ ከጥፋት ጋራ፣ ምሥጋናን ከማጉደል ጋራ፣ ካለማመን ጋራ፣ በሀሰት ከመማል ጋራ። በጎውን ሰው ከማወክ ጋራ፣ እግዚአብሄር የሚሰጠውን ዋጋ ካለማሰብ ጋራ፣ ፍጥረትን ከመለወጥ ጋራ፣ የግቢን ሥርዐት ከማፍረስ ጋራ፣ ከምንዝር ጋራ፣ ከሚያፀይፍ ሥራ ጋር የተቀላቀለ ነው። <u>ስም የሌላቸው ጣዖቶችን ማምለክ የክፉት ሁሉ መጀመሪያ ነውና፣ የሀጢያትም ፍፃሜ ነውና፣</u> የሚያመልኳቸው ሰዎች እንደነዚህ ደስ ቢላቸው አእምሯቸውን ያጣሉና፣ ልጆቻቸውን ይሰዋሉ። (መፅሐፈ ጥበብ፣ ም.14.ቁ. 22፣ ቁ. 25 - 27)*

## ክፍል ስድስት

### መሸበቢያ

<u>**በቅድሚያ፣**</u>

የመለስ "ትሩፋቶች"፣ ባለቤት አልባ ከተማ! በዋናነት የታሪክ ውቅሩ አዲስ አበባን ያማከለ ነው። በሶስት ምርጫዎች (በ92፣ 97 እና 2000 ዓ/ምቶች) የነበረውን የኢትዮጵያ ሶሺዮ ፖለቲካ ትኩሳትና ብርደት፣ ውጥረትና እርግበት፣ ሞትና ህመም እንደ ተንቀሳቃሽ ፊልም በሥነ ፅሁፍ ቀርፆ የወጣ። ስምንት ዐበይት ክፍሎች፣ ሃያ ስምንት ምዕራፎች፣ በአያሌ ንዑስ ርዕሶች ተዋቅረው በ405 ገፆች ተጠርዘው በነፃነት አሳታሚ ድርጅት በ2006 ዓ/ም፣ እንደ ፈረንጁ ቆጠራ ደግሞ በ2014 በሀገረ አሜሪካ የታተመ።

በዚህ ቅኝት ይህ ክቡድ የታሪክ መረጃ/ኤግዚቢት መፅሀፍ በቂ ዳሰሳ ተደርጎበታል ብሎ የሚያስብ የዚህ ፅሁፍ ታዳሚ ካለ በእጅጉ ከዕውነታው የራቀ መሆኑን በትህትና ልናመለክት እንወዳለን።

*መፅሀፈ ኤርምያስ* (እኛ በተለዋጭ ስም እንደምንጠራው) ለዝርዝር የሚበዙ የታሪክ ዝርዝሮችን ያቀረበ፣ ከዚህ ቀደም፣ በዚህ መንግሥት (ህወሃት መራሹ ኢህአዴግ) ዕኩይ ተግባራት ላይ ለሕዝብ ያልቀረቡ አሳዛኝ፣ ዘግናኝ፣ በቁጭት የሚያበግኑ፣ የጥፋትና

የምዝበራ፣ የግፍና ተንኮል ተግባራት እርቃናቸውን የወጡበት ሥራ ነው፣ በበቂና በማያነቃንቁ መረጃዎች።

በጨፌው ግምገማ የሚጀምረውና የጉድ ታሪክ የጎለጎለው ክፍል ሰፊና ጥልቅ ነው። ‘በባህታዊው’ ህወሃቱ የሚመራውና በአዲስ አበባው ፕሬዚዳንት አሊ አብዶ ሥራ ፈፃሚነት የተተገበረው የጨለማው ዘመን ዘመነ መሳፍንት የካዛንችሱ መንግሥት ሥውር ታሪክ አንባቢን ለቁርጠት እስከመዳረግ ያደርሳል። ዘረፋው፣ ብዝበዛው…ጉድ ያሰኛል።

“የዘመቻ ጨረቃ መውጣት” ታሪክ ደግሞ ተአምር ነው። መልዕክተ ኤርምያስ በስፋት አስተላልፎታል። ይህንን ጥልቅ ዘርፊ ብዙ የግፍ ታሪክ ሲያነቡ፣ ኢትዮጵያ ‘በጉግ ማንጉግ’ ዘመን ውስጥ አልገባችም ለማለት ከቶም የሚደፍር አንደበት አይገኝም። መረን ከለቀቀው የመሬት ዝርፊያ ባሻገር፣ በህዝቡ ላይ የደረሰው የሰቆቃ ዝርዝር ልብን ይሰብራል፣ መንፈስን ይረብሻል። ይህም ታሪክ በስፋት ተላልፏል፣ ከነመረጃዎቹ።

በዚህ የጨለማው ንጉሥ ዘመን ዘመነ መሳፍንት ታሪክ ውስጥ በኪዳነ ምህረት ቤተ ክርስቲያን ታቦት መውጫ ሜዳ ላይ የተሰራውን ዘግናኝ ወንጀል መረዳት የሚቻለው መፅሀፊ ኤርምያስን በማንበብ ብቻ ነው!! ታሪኩ ሲፈፀም እንኳን እኛ በታሪክነት ስናነበው ከአለማመን ብዛት አስሬ የምናማትበው ቀርቶ በወቅቱ በቦታው የተገኘው ኤርምያስ ራሱ ‘ሰማይና ምድሩ’ ጨልሞበት ነበርና…

የ‘ጉራጌ መራሹ’ አብዮትና አከሻሸፉ ታሪክ ደግሞ በዚህ መንግሥት ታሪክ ውስጥ ህዝብ በይፋ ከማያውቃቸው ታሪኮች አንዱ ሆኖ ይገኛል። የጦላይ ተጋዳሊቶች ታሪክ ደግሞ ያስደምማል። በዚህና በተጓዳኝ ታሪኮች ላይ የቀረበው የህወሃት ‘ዲሞብላይዝድ’ ሠራዊት ታሪክ በመጪዋ ኢትዮጵያ ህልውና ላይ ከሚያንዣብቡት ‘ጎረቤት’ በቀል አደጋዎች አንዱና ዋነኛው ሊሆን ይችላል ብለን እናምናለን።

እኒህ ከነጦር መሳሪዎቻቸው ‘ዲሞብላይዝድ’ የሆኑት (ጡረታ የወጡት) ከአስር ሺህ በላይ የቀድሞ የህወሃት ተጋዳሊቶችና ተጋዳዮች የሲቪል ልብሳቸውን ቂቅ አድርገው፣ በሲቪል መሥሪያ ቤቶች ተሰግስገው በህዝብ መኻል ይገኛሉ። በየቤቶቻቸው የተከማቸ ጦር መሳሪያዎች ዝግጁ ሆነው ተቀምጠዋል። ‘የነገን ማን ያውቃል?” ብለው። ይህ በእጅጉ ማንኛውንም ሀገር ወዳድ ዜጋ ሊያሳስብ የሚገባው ብቻ ሳይሆን እኒህ “ጡረተኛ” የሠራዊቱ አካላት እነማን እንደሆኑና የትስ እንደሚኖሩ የማወቅ እና የማጋለጥ ሃላፊነት ሥርዐቱን ለመለወጥ የሚታገሉ ሁሉ ከቅድሚያ የቤት ሥራዎቻቸው መኻል አንዱና ዋናው ሊሆን ይገባል እንላለን። ከህወሃት ሠራዊት ባልተናነሰ በቀውጢ ቀን እኒህ ‘ጎረቤት’ ታጣቂ ህወሃታውያን የሚያደርሱት የእልቂት ዝናብ በቀላሉ ሊታይ የሚገባው አይደለምና!

መፅሀፊ ኤርምያስ ይፋ ካደረጋቸው አሳዛኝ ታሪኮች አንዱ ሀገሪቱ የምትገኝበት የትምህርት ደረጃ ነው። የልጆቻቸውን ስም አስተካክለው መፃፍ የማይችሉ ህወሃታውያን በኢኮኖሚክስ እና በሊደርሺፕ ዲግሪዎች የተንበሸበሹ መሆናቸውን ከነሰዎቹና ከነመረጃዎቹ ዘርግፎት ስናየው፣ የዶክትሬት ተመራቂ ህወሃት/ኢህአዴጋውያንን ታሪክም አዳብሎ ሲተርክልን ‘እንግዲህ ይህቺ አገር ምን ተረፋት?” ከማለት አልፈን በትልቅ ሀዘን ውስጥም እንድንገባ ያደርገናል፣ ዙሪያው ገደል ሆኖብን። ከሁሉም በላይ ግን፣ በቀኝ እጁ መፅሀፍ ቅዱስ፣ በግራ እጁ ደግሞ የዘርፈውን ዶላር ይዞ፣ ህወሃት/ኢህአዴጎችን በዲግሪ የሚያንበሸብሸው የጴንጤቆስታል ዕምነት ዘርፍ ሰባኪ የፓስተር ባደግ ታሪክ በሀገሪቱ ላይ የሰፈሩትን የጅቦች አይነትና ስብጥር አግዝፎ ከማሳየት አልፎ፣ ህሊናን በእጅጉ ያቆስላል።

የፓስተር ባደግ ተግባር በዘመነ ኮሎኒያሊዝም አፍሪካን አውሮፓውያን ሲቀራመቷት፣ ከነፃነት ታጋዮች አንዱ እንደ ፓስተር ባደግ ያሉትን ኮሎኒያሊስት

ሰባኪያን ሲገልፅ፣ ‘እኛን ወደ ሰማይ እንድናንጋጥጥ እያደረጉ፣ እነሱ ከእግራችን ስር መሬታችንን ወሰዱት’ ማለቱን እንድናስታውስ አድርጎናል። ይህ የቀድሞው ኮሎኒያሊስቶች ታሪክ በዛሬይቱ ‘በመለስ ራዕይ’ በምትመራዋ ኢትዮጵያ በተግባር እየሆነ ይገኛል። ሀገሪቱ በባዕዳን ‘ባለሀብቶች’ በተለይም በሳውዲዎች እጅ ወድቃለችና። ለአባባላችን ጥልቀት መልዕክተ ኤርምያስን ይጋብዟል።

የአዲስ አበባን ማስተር ፕላን አስመልክቶ ከመመሪያ ቁጥር አንድ እስከ መመሪያ ቁጥር ሶስት (ከፕሬዚዳንት አሊ አብዶ አስከ ከንቲባ አርከበ እቁባይ እስከ ከንቲባ ኩማ ደመቅሳ) መሬት ዘራፊዎችን ከህገ ወጥነት ወደ ህጋዊ ዘራፊነት የማሸጋገርን ተግባርና ሂደት ኤርምያስ ቋጠሮዎቹን እየፈታ መረጃዎቹን ሲደረድር እንግዲህስ ምን ቀረን? በእንደምን ያለ መንግሥትስ እጅ ውስጥ ነው ይህቺ አገር የወደቀችው? በማለት እንድንብከነከን ያደርገናል። ስለ መመሪያ ቁጥር አራት ያነሳው ደግሞ ራሱን የቻለ ድርና ማግ ያለው እጅግ አሳሳቢ ታሪክ ሆኖ እናገኘዋለን።

በአዲስ አበባ ዙሪያ የሚገኙ የኦሮሞ ክልሎችን በማስተር ፕላኑ ለማካተት መመሪያ ቁጥር አራትን ከመተግበር አኳያ እርስ በርሳቸው የሚፋጠጡ ሶስት አንጃዎች መኖራቸው፣ ከነዚህም አስጊው አንጃ በአባዱላ ገመዳና በምክትል ፕሬዚዳንቱ አብዱላዚዝ የሚመራው መሆኑን ይነግረናል፣ መልዕክተ ኤርምያስ። እነ አባዱላ ገመዳና አብዱላዚዝ በእነዚህ የኦሮምያ ክልሎች የገነቡዋቸው ህንፃዎችና የዘረፉት መሬት የትየለሌ ከመሆኑም ባሻገር የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃና ዩዩኒቨርሲቲ፣ ኮሌጅ ተማሪዎችንና መምህራንን በኦህዴድ ካድሬዎች በኩል የተቆጣጠሩዋቸው (በፈለጉ ወቅት ሊያነሷሷቸው የሚችሉ) መሆናቸውን ይገልፃል።

ማስተር ፕላኑ በመመሪያ ቁጥር አራት በሌሎቹ ሁለት አንጃዎች (አንደኛው በህይወት በሌለው መለስ፣ በስምዖን ልጅ በረከት፣ በኩማ ደመቅሳ፣ ሙክታር ከድርና አስቴር ማሞ…የሚመራ፣ ሌላኛው ደግሞ አዲስ አበባን በአጥንቷ ባስቀራትና የህወሃት ባለሀብቶችን በመፍጠር ቀንደኛው አስፈፃሚ አርከበ እቁባይ፣ ሚኒስትር መኩሪያ ሃይሌና በአዲስ አበባ ሥራ አስኪያጅ ሀይሌ ፍሰሃ የሚመራ ሲሆን፣ የዜናዊ ባለቤት አዜብ መስፍን የዚህ አንጃ ደጋፊ ናት። ሁለቱ ቡድኖች ተደጋጋፊ ህወሃት በቀል ግብ ነው ያላቸው) የሚተገበር ከሆነ እነ አባዱላ ዘመነ መሳፍንት አገዛዛቸው ያፈራላቸውን ሀብትና ንብረት ከህወሃት ነጠቃ ለመከላከል ሲሉ መመሪያ ቁጥር አራትን በመቃወም በተማሪዎችና መምህራን አማካይነት ሊያስነሱት የሚችሉት ነውጥ ቀላል አይደለም ይላል።

እንግዲህ ታዲያ በአዲስ አበባ ማስተር ፕላን አፈፃፀም ላይ በቅርቡ - በአንቦና በአካባቢው ተነስቶ በነበረው አመፅና ይህንንም አመፅ ተከትሎ በጠፋው ህይወት ውስጥ የነ አባዱላ እጅ ይኖርበት ይሆን? ተቃውሞውንና ህይወት መጥፋቱን ተከትሎም ሌሎቻችን ያሰተጋባነው ተቃውሞ (ምንም እንኳን መደረግ የነበረበት ቢሆንም) የእነባዱላን አጀንዳ ባለማወቅ እየደገፍን ነበር እንዴ? ብለን እንድናሰላስል ያስገድደናል። በዚህ አይነት የትግሉንም አጀንዳ እየቀረፁ ይሆን እንዴ “የሚያታግሉን”? ማለታችንም አይቀርም።

ራሱ ኤርምያስ የተሳተፈበት የቅዱስ ሲኖዶስ ስብሰባ ታሪክና ያነገቡት ተልዕኳቸው ለሰማይም ለምድርም የከበደ እንደ መቃብርም የሚያስፈራ ታሪክ ነው። መልዕክተ ኤርምያስ እንደገለፀው በእስልምናው ሃይማኖትም መጅሊሱ የህወሃት/ኢህአዴግ መጅሊስ ይመስላል ሲል ከነመረጃዎቹና ተዋናዮቹ (እኒህ በቅዱስ ሲኖዶሱም ውስጥ ተዋናይ ናቸው) ይዘረዝራል፣ ዝርዝሩን ከምንጩ ይሰበስቧል።

እነሆ እንግዲህ - የመለስ “ትሩፋቶች” ባለቤት አልባ ከተማ፣ እኒህንና በዚህ “የሶምሶማ” ቅኝት ያልተነቀሱ ሌሎችንም በርካታ የታሪክ ሰበዞች ያነገበ ሰነድ ነው። የህወሃት መራሹ ኢህአዴግ መንግሥት የታሪክ ጉድፍ ይፋ የወጣበት መረጃ!!

## በማስከተል፣

*ሀገሬ ኢትዮጵያ ኖት እኔም ኢትዮጵያዊ ነኝ የምትል የተስፋይቱ ምድር ልጅ ሆይ!* እነሆ፣ ‘ፖለቲካና ከረንቲን በሩቅ’ የምትልም ቢሆን፣ ወይም ‘ህይማኖቴ ፖለቲካ ይከለክለኛል’ የምትልም ቢሆን፣ ወይም የህወሃት/ኢህአዴግ ደጋፊ ነኝ የምትልም ቢሆን፣ ወይም የኢህአዴግ አባል/ካድሬ ነኝ የምትልም ቢሆን፣ ወይም ኢንቨስተር ነኝና ፖለቲካ አይመለከተኝም የምትልም ቢሆን፣ ወይም በድፍኑ የመንግሥት ተቃዋሚ ነኝ የምትልም ቢሆን፣ ወይም ‘ይህም ሄደ ያም መጣ’ ያው ‘በገሌ ነው’ የምትልም ቢሆን፣ ወይም የቁርዐን ተከታይ ነኝ የምትልም ቢሆን፣ ወይም ዕምነቴ መፅሀፍ ቅዱስ ነው የምትልም ቢሆን፣ ወይም በፈጣሪም ሆነ በዕምነት አላምንም የምትልም ቢሆን፣...ስለራስህ ስትል ብቻ *መፅሀፈ* ኤርምያስን፣ “የመለስ ትሩፋቶች - ባለቤት አልባ ከተማ”ን - አንብብ!!

## ማሳረጊያ፣

ኤርምያስ ሆይ ደግመህ ፃፍ! በግፍዕ ዘመን ያየኸውንና የፈፀምከውን ሁሉ ፃፍ። ስለ ሕዝብህ ዋይታና ግፍ፣ በደልና ጭቆና፣ ስለአፈፃፀሙም ዝግነና ተናዘዝ። ስለሀገርህ መመዝበር፣ ስለታሪኳ መዋረድ፣ ስለአባቶችህና እናቶችህ የታሪክ አሻራ መና መቅረት...የተደረገውንና ያደረግኸውን፣ ያየኸውንና የሰማኸውን ሁሉ ተናዘዝ።

ኤርምያስ ሆይ በርታ፣ ኤርምያስ ሆይ በርታና አንዳች ሳታስቀር ተናዘዝ! የተጨነቀች ነፍስህ ሠላም፣ የዋተተች ሕይወትህ መልህቅ ታገኝ ዘንድ! ከሀገርህ የእናት ይቅርታ፣ ከወገንህ የጠፋው በግ እቅፍታ ታገኝ ዘንድ!

ኤርምያስ ሆይ በልቡናህ የተጠራቀመውን ሁሉ ተናዘዝ። እነሆ ደራሲ ነፍስህ ራሷን ነፃ እንዳወጣች፣ እንግዲህ ደግሞ ሌሎችን ነፃ ታወጣ ዘንድ ብቸኛ ሃይሏ የተቀበረች ሀቅን ነፃ ማውጣት ነውና መልዕክተ ኤርምያስ ሁለተኛን ደግሞም ሶስተኛን ለጦቢያ ልጆች ምሥክር ሆና ትናገር! ‘በመለስ ራዕይ’ እና ‘በትንቢተ ስምየን’ እግረ ሙቅ ተተብትበው በአብዮታዊ ዲሞክራሲ ድንኳን ለተሰበሰቡትም እነሆ ነፍስህ ድምጿን ታሰማ፣ “የፍፃሜው ዘመን ቀርቧልና፣ የመዳንም ተስፋ ቀንበሩን መስበር ነውና፣ ቀንበሩን ከትከሻችሁ አውርዱ፣ ወደ እትብታችሁ ትመለሱ ዘንድ” ትበል።

አዎ ዕውነት ነው! በእኛ በኩል *መፅሀፈ* ኤርምያስ ቀዳማይ በነገረን ሁሉ ተጨንቀናል፣ አልቅሰናል፣ ታመናል፣ ወዮ! ብለን ጮኸናል። ስለ ሥራህ ሳይሆን ሥራህ ስለፈጠረብን ውስጠ ቃጠሎና ቁጭት ደግሞ ወደንሃል። ከጭንቀታችን ማዶ - ተስፋ፣ ከልቅሶችን ማዶ - ፍሰሃ፣ ከህመማችን ማዶ - ፈውስ፣ ከጩኸታችን ማዶ - እፎይታ፣ ይታየናልና! አዎ! ሲነጋ ሲል ይጨልማልና፣ መንጋቱም ይታወቀናልና።

ኤርምያስ ሆይ፣ “የመለስ ትሩፋቶች - ባለቤት አልባ ከተማ”ን ስላስነበብከኝ እነሆ ልባዊ ምሥጋናዬ ይድረስህ።

------------------ተፈፀመ--------------------

በያለንበት ቸር ይግጠመን!
ህዳር፣ 2007 ዓ/ም
ኖቬምበር 2014
ሲድኒ፣ አውስትራሊያ

አስተያየት ቢኖርዎ፣ የመልዕክት አድራሻዬ ይኸውልዎ mmtessema@gmail.com